# የእይታና የትወና ጥበባት

## የተማሪ መጽሐፍ



## 3ኛ ክፍል

የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ

# ውድ ተማሪዎች



## ለዚህ መማሪያ መጽሐፍ ተገቢውን እንክብካቤና ጥበቃ አድርጉ...

**ይህ መማሪያ መጽሐፍ የትምህርትቤታችሁ ንበረት ነው። መጽሐፉ እንዳይበላሽ ወይም እንዳይጠፋ በጣም መጠንቀቅ አለባችሁ። መጽሐፉን በጥንቃቄ ለመያዝ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን 10 መመሪያዎች ተግባራዊ አድርጉ።**

1. መጽሐፉን ከጉዳት ለመከላከል በላስቲክ ወይም በወረቀት ሸፍኑት።
2. መጽሐፉን ሁልጊዜ በደረቅና በንጹህ ቦታ አስቀምጡት።
3. መጽሐፉን ለመጠቀም ስትዘጋጁ በቅድሚያ እጃችሁ ንጹህ መሆኑን አረጋግጡ።
4. በመጽሐፉ ሽፋን ወይም የውስጥ ገጾች ላይ አትጻፉ።
5. በመጽሐፉ ገጾች መካከል እልባት ለማድረግ ስትፈልጉ ብጣሽ ወረቀት ክር ወይም ካርድ ተጠቀሙ።
6. በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ሥዕሎች ወይመ ገጾች በፍጹም አትቅደዱ።
7. በመጽሐፉ ውስጥ የተቀደደ ወይም የተገነጠለ ገጽ ሲኖር በሙጫ ወይም በሌላ ንጽህ ማጣበቂያ አጣብቁት።
8. መጽሐፉን ከቦርሳችሁ ስታስገቡ ወይም ስታወጡ ጥንቃቄ አድርጉ።
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው ስታቀብሉም ሆነ ከሌላ ሰው ስትቀበሉ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጉ።
10. መጽሐፉን ለመጀመሪያ ጊዜ ስትጠቀሙ ሽፋኖቹና ገጾች እንዳይገነጠሉ መጽሐፉን በጀመርባው ጋደም አድርጋችሁ አስቀምጡት ከዚያም ጥቂት ግጾችን ቀስ እያላችሁ በየቀሩ ግለጡ በግራና በቀኝ እጃችሁ የያዛችሁትን የመጽሐፉን ክፍል በኃይል አቅጫኑት (አትመንጭቁት)።

# የእይታና የትወና ጥበባት

## የተማሪ መጽሐፍ

## ሶስተኛ ክፍል


**አዘጋጆች:-**

- ወርቅነ ሃ/ሚካኤል
- አዉታሩ አራጎ
- ምስራቅ ፀሃይ
- ታምራት አብራሃም

**ሰዓሊ:-**

- ወርቅነህ ሃ/ሚካኤል

**ኤዲተር:-**

- ፍቃዱ ደጀኔ
- ጥራት ተቆጣጣሪ(ፓናሊስት):-
- ተዋበ ታደሰ
- ተክለማሪያም ጥላሁን

**አፅዳቂ:-**

- ተስፋዬ እሸቱ
- ሲዳማ ስላሴ
- ዋንቱሳ ጎንሳ
- ይመኙሻል ዮሴፍ
- ሀብታሙ ጳውሎስ
- ቅድስት ደፋር

**ዲዛይንና ሌይአውት:-**

- ሲሳይ ታገሠ



2015 ዓ.ም

የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ትምህርት ቢሮ

# © ቅጂ መብት

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በኩል በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ሲሆን የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስተርና የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ እና በዲላ ትምህርት ኮሌጅ የቴክኒክ ድጋፍ በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀ ሲሆን አጠቃላይ የሕትመት ወጪው በደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ተሸፍኗል፡፡

የመጽሃፉ ሕጋዊ ቅጂ ባለቤት © 2014 ዓ.ም የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስተርና የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ናቸው፡፡

2014 ዓ.ም

ሀዋሳ

# ማውጫ

**ምዕራፍ አንድ ........................................ 1**

**1. መለየትና መግለፅ ........................................ 1**

1.1. የሙዚቃ ኖታዎች እስከ እሩብ ኖታ እና እሩብ እረፍት ድረስ ........................................ 2

1.2. መሰረታዊ ቀለማት ........................................ 10

1.3. ቀለል ያለ ግለ-ተውኔት እንዲሁም ፎቶ ማንሳትና የዳንስ ስነ-ምግባር ........................................ 14

የምዕራፍ ማጠቃለያ ........................................ 20

የማጠቃለያ ጥያቄዎች ........................................ 20

**ምዕራፍ ሁለት ........................................ 1**

**2. የተግባር ልምምድ ........................................ 1**

2.1. ድምፅ፣ ሙዚቃ፣ ኖታዎች እና የምት ሙዚቃ መሳሪያዎች ........................................ 2

2.2. ቀላል የሆኑ ዝርግ ቅርጾችን ባለሁለት እና ሦስት አውታር መጠን ቅርጾችን መንደፍ እና ማቅለም ........................................ 10

2.3. መሰረታዊ ቀለማትን መቀላቀል እና ቀጥታ ህትመት ........................................ 14

2.4. በተውኔት፣ በተንቀሳቃሽ ምስሎችና ፎቶዎች መልዕክቶችን ማስተላለፍ ........................................ 18

የትምህርቱ ማጠቃለያ ........................................ 25

የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች ........................................ 26

**ምዕራፍ ሦስት ........................................ 1**

**3. ባህላዊ አውድ ........................................ 1**

3.1. ባህላዊ ብዝሀነት ባለፈው እና በአሁኑ ጊዜ በእይታና የትውን ጥበባት ሲቃኝ ........................................ 2

የምዕራፍ ማጠቃለያ ........................................ 13

የማጠቃለያ ጥያቄዎች ........................................ 14

**ምዕራፍ አራት ........................................ 1**

**4. አድናቆት ........................................ 1**

4.1. ሀገረሰባዊ ጥበባት በትውን እና እይታ ጥበባት በኢትዮጵያ ........................................ 2

ማጠቃለያ ........................................ 9

የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች ........................................ 10

**ምዕራፍ አምስት ........................................ 1**

**5. የቡድን ተግባር (ግንኙነት፤ ተግባቦት እና ተግባር) ........................................ 1**

5.1. የትውንና የእይታ ጥበባት እርስ በርስ ያለው ዝምድና ........................................ 2

ማጠቃለያ ........................................ 8

የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች ........................................ 8

**ዋቢ መፅሐፍት ........................................ 10**

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መለየትና መግለፅ

### መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ የሦስተኛ ክፍል ተማሪዎች በእይታ እና ትውን ጥበባት ትምህርታቸውን የሙዚቃ የኖታ ምልክቶችን ፣ የእረፍት ምልክቶችን እስከ እሩብ ኖታ እና እሩብ እረፍት ድረስ ያሉ ምልክቶችን ቅርፅ እና አፃፃፍ የሚለዩበት፡፡ መሰረታዊ ቀለማት እነማን እንደሆኑ በስም እና በመልክ የሚለዩበት፡፡ በቀላሉ ፎቶ ማንሳት እና ምጥን ተውኔት ምን እንደሆኑ እንዲረዱ እና እንዲለዩ በማሰብ ለዚህ ክፍል ደረጃ አንዲመጥን ተደርጎ ቀርቧል፡፡

በመሆኑም ተማሪዎች በየንዑስ ክፍለ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱትን ፅሑፎች እና ስዕላዊ መግለጫዎች በሚገባ በማንበብ እና በመገንዘብ ፣ በየንዑስ ክፍለ ትምህርቱ የቀረቡትን የመልመጃ ጥያቄዎች በመስራት የተፈለገውን ውጤት ያመጣሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡

### ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

- የሙዚቃ ኖታዎችን እስከ ሩብ ኖታ እና እሩብ እረፍት ድረስ ይለያሉ
- መሰረታዊ ቀለማትን ይለያሉ
- በቀላሉ ፎቶ ማንሳትን እና ምጥን ተውኔትን ይረዳሉ

# 1.1. የሙዚቃ ኖታዎች እስከ እሩብ ኖታ እና እሩብ እረፍት ድረስ

## መግቢያ

በምንኖርባት ዓለም ውስጥ ያሉ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ የራሳቸው ሙዚቃ አላቸው፡፡ ይህም ማለት ያለ ሙዚቃ የሚኖር ማህበረሰብ በምድራችን ውስጥ የለም ማለት ነው፡፡ ሙዚቃ ሰዎች አስተሳሰባቸውን ፣ ፍላጎታቸውን ፣ አኗኗራቸውን ፣ ሃዘናቸውን ፣ ደስታቸውን ወ.ዘ.ተ. ከሚገልፁባቸው መንገዶች ውስጥ አንደኛው የጥበብ ውጤት ሙዚቃ ነው፡፡ በርካታ የአለማችን ሰዎች ሙዚቃ የዓለም ቋንቋ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ይህ ሙዚቃ የዓለም ቋንቋ ነው የሚለውን ቃልም በሁለት መንገድ ተርጉመን እናየዋለን፡፡ አንደኛ ሙዚቃ የዓለም ቋንቋ ነው ስንል አንድ ከማንኛውም ማህበረሰብ ክፍል የሚኖር ሰው በሌሎች ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ሙዚቃ በመስማት (በማዳመጥ) የማህበረሰቡን የአኗኗር ዘይቤ ፣ እምነት ፣ በሀዘን ወይም በደስታ ስሜት ውስጥ መሆኑን እና የተለያዩ ማህበረሰባዊ ጉዳዮችን በቀላሉ ከሚሰሩት ሙዚቃ ለመረዳት የሚያስችል ነው፡፡ በሁለተኛ ሙዚቃ የዓለም ቋንቋ ነው የምንለው ደግሞ እንደማንኛውም የንግግር ቋንቋዎች አማርኛ ፣ ጋሞኛ ፣ ጎፍኛ ፣ አላባኛ ፣ ዳዉሮኛ ፣ ወላየትኛ ወ.ዘ.ተ. ሁሉ ሙዚቃም የራሱ የሆነ ፊደላት ያሉት ፣ የሚፃፍ ፣ የሚነበብ ፣ በድምፅ ወይም በሙዚቃ መሳሪያ ልሳን የሚነገር እና በጆሮ የሚደመጥ በመሆኑ ሙዚቃ የአለም ቋንቋ ነው እንላለን፡፡

### ከዚህ ንዑስ ክፍለ ትምህርት በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

- የሙሉ ኖታ እና ሙሉ ዕረፍት ምልክቶችን ይለያሉ፡፡
- የሙሉ ኖታ እና ሙሉ እረፍት ምልክቶችን ትርጉም ይገልፃሉ፡፡
- የሙሉ ኖታ እና የሙሉ እረፍት ምልክቶችን ቅርፅ ይለያሉ፡፡
- የግማሽ ኖታ እና ግማሽ እረፍት ምልክቶችን ቅርፅ ይለያሉ፡፡
- የሩብ ኖታ እና የሩብ እረፍት ፣ ምልክቶችን ቅርፅ መለየት፡፡
- የሩብ ኖታ እና የሩብ እረፍት ፣ ምልክቶችን መፃፍ እና ማንበብ፡፡

**የመወያያ ጥያቄ፡-**

1. ከአሁን በፊት ስለ ሙዚቃ ኖታዎች የነበራችሁ ግንዛቤ ምን ነበር?
2. የሙዚቃ ኖታዎች ምን አይነት ጥቅም አላቸው?
3. የሙዚቃ ኖታዎች የምንላቸው ምንድን ናቸው?

## 1.1.1. ሙሉ ኖታ እና ሙሉ እረፈት ግማሽ ኖታ እና ግማሽ እረፍት

### 1. ሙሉ ኖታ እና ሙሉ እረፍት

ከዚህ በታች የተቀመጠውን ሰንጠረዥ በመጠቀም የኖታወች ቅርፅ ምን እንደሚመስሉ ማየት እንችላለን፡፡

ሰንጠረዥ 1.1:


| የኖታ ምልክት | የምልክቱ ስም | የሚሰጠው ዋጋ (የጊዜ ቆይታ) | የእረፈት ምልክት | የምልክቱ ስም | የሚሰጠው ዋጋ (የጊዜ ቆይታ) |
|---|---|---|---|---|---|
| 𝅝 | ሙሉ ኖታ | 4 ምቶች ያሉት ሲሆን በአንድ ትንፋሽ በድምፅ መቁጠር | 𝄻 | ሙሉ ዕረፍት | 4 ዕረፍቶች ያሉት ሲሆን በዝምታ (ድምፅ አልባ) ሆኖ ይቆጠራል |

**ሀ. ሙሉ ኖታ፡-** ሙሉ ኖታ የምንለው ምልክቱ ( 𝅝 ) ክብ ወይም ዜሮ ቅርፅ ሲሆን በአንድ ትንፋሽ አራት ምቶችን ያለማቋረጥ መጫወትን የሚወክል ነው፡፡

### የተግባር ልምምድ -1

1. ከታች ያለውን የቀስት ምስል በመከተል እጃችሁን በእርጋታ እና በእኩል የጊዜ ቆይታ በማወዛወዝ የኖታ ምልክቱን በትክክል መቁጠር ተለማመዱ፡፡

○ አራት ምት ድምፅ መጫወት




አንድ ሙሉ ኖታ ( ○ ) ሁለት ግማሽ ( 𝅗𝅥 + 𝅗𝅥 ) ኖታወች ተደምረው ከሚሰጡት የጊዜ ቆይታ ጋር እኩል ዋጋ አለው።

**ምሳሌ፡-** 𝅗𝅥 + 𝅗𝅥 = ○


ሁለት ምት + ሁለት ምት = አራት ምት

## ለ. ሙሉ ዕረፍት፡- ( 𝄻 )

አራት ምቶች ያሉት ሲሆን በዝምታ (ድመፅ አልባ) ሆኖ ይቆጠራል። አንድ ሙሉ እረፍት( 𝄻 )ሁለት ግማሽ እረፍት ( 𝄼 + 𝄼 ) ተደምረው ከሚሰጡት የጊዜ ቆይታ ጋር እኩል ዋጋ አለው።

**ምሳሌ፡-** 𝄼 + 𝄼 = 𝄻 አራት ምት እረፍት

2 እረፍት + 2 እረፍት = 4 እረፍት



## የተግባር መልመጃ 1

1. ከዚህ በታች የተፃፉትን አምስት ባለ ሙሉ ኖታ የድመፅ ምልክት ትክክለኛውን የጊዜ ቆይታቸውን (ዋጋቸውን) በመስጠት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው?
2. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን አምስት ባለ ሙሉ እረፍት (ድምፅ አልባ) ምልክቶችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው?

## መልመጃ 1

**ከዚህ በታች ለተዘረዘሩ ጥያቀዎች ተገቢውን መልስ ስጡ**

1. የእረፍት ምልክቶች የምንላቸው ምንን ይወክላሉ?
2. የኖታ ምልክቶች የምንላቸው ምንን ይወክላሉ?
3. አንድ ሙሉ ኖታ ምን ያህል ድምፅ ቆይታ አለው?
4. አንድ ሙሉ የእረፍት ምልክት ምን ያህል የድምፅ ቆይታ አለው?

## 2. ግማሽ ኖታ እና ግማሽ እረፍት

**ሀ. ግማሽ ኖታ፡-** ( 𝅗𝅥 ) በአንድ ትንፋሽ ሁለት ምቶችን ያለማቋረጥ መጫወትን የሚወክል ነው፡፡ ግማሽ ኖታ(𝅗𝅥) ሁለት ሩብ ኖታወች (♩+♩) ተደምረው ከሚሰጡት የጊዜ ቆይታ ጋር እኩል ዋጋ አለው፡፡


ሰንጠረዥ 1.2:

| የኖታ ምልክት | የምልክቱ ስም | የሚሰጠው ዋጋ (የጊዜ ቆይታ) | የእረፈት ምልክት | የምልክቱ ስም | የሚሰጠው ዋጋ (የጊዜ ቆይታ) |
|---|---|---|---|---|---|
| 𝅗𝅥 | ግማሽ ኖታ | 2 ምቶች ያሉት ሲሆን<br>በአንድ ትንፋሽ መቁጠር | 𝄼 | ግማሽ እረፍት | 2 እረፍቶች ያሉት ሲሆን<br>በዝምታ (ድምፅ አልባ) ሆኖ ይቆጠራል |

## የተግባር ልምምድ -2

ከታች ያለውን የቀስት ምስል በመከተል እጃችሁን በእርጋታ እና በእኩል የጊዜ ቆይታ በማወዛወዝ የኖታ ምልክቱን በትክክል መቁጠር ተለማመዱ::

የድ.መነሻ ነጥብ 𝅗𝅥 የድ.መድረሻ ነጥብ




መሃል መሃል

**ለ. ግማሽ እረፍት** ( 𝅗𝅥 ) ሁለት ምቶች ያሉት ሲሆን በዝምታ (ድመፅ አልባ) ሆኖ ይቆጠራል:: ግማሽ እረፍት ( 𝄼 ) ሁለት ሩብ እረፍት (♩ + ♩) ተደምረው ከሚሰጡት የጊዜ ቆይታ ጋር እኩል ዋጋ አለው::

የእረፍት.መነሻ ነጥብ 𝄼 የእረፍት.መድረሻ ነጥብ

1 2



መሃል መሃል

## የተግባር መልመጃ 3

1. ከላይ በተገለፀው መሰረት ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን አምስት ባለ ግማሽ ኖታ (ባለ ድምፅ) ምልክቶችን በመቁጠር ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው::

𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅗𝅥

2. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን አምስት ባለ ግማሽ እረፍት (ድምፅ አልባ) ምልክቶችን ቁጠሩ



## 3. እሩብ ኖታ እና እሩብ እረፍት

በመቀጠል ደግሞ ከታች የተቀመጠውን ሰንጠረዥ በመጠቀም እሩብ ኖታ፣ እሩብ እረፍት፣ 1 ኖታ እና 1 እረፍት ምልክቶችን ቅርፅ እና የጊዜ ቆይታቸውን እንመልከት።

ሰንጠረዥ 1.3:


| የኖታ ምልክት | የምልክቱ ስም | የሚሰጠው ዋጋ (የጊዜ ቆይታ) | የእረፍት ምልክት | የምልክቱ ስም | የሚሰጠው ዋጋ (የጊዜ ቆይታ) |
|---|---|---|---|---|---|
| ♩ | ሩብ ኖታ | 1 ምት ያለው ሲሆን በአንድ ትንፋሽ በድምፅ መቁጠር | 𝄽 | ሩብ እረፍት | 1 ምት ያለው ሲሆን በዝምታ (ድምፅ አልባ) ሆኖ ይቆጠራል |

**ሀ. እሩብ ኖታ፡-** ( ♩ ) አንድ ምት መጫወትን የሚወክል ነው።

## የተግባር ልምምድ 1

1. ከታች ያለውን የቀስት ምስል በመከተል እጃችሁን በእርጋታ እና በእኩል የጊዜ ቆይታ በማወዛወዝ የኖታ ምልክቱን በትክክል በመቁጠር ተለማመዱ።

የድ.መነሻ ነጥብ ♩ የድ.መድረሻ ነጥብ




መሃል

**ለ. ሩብ እረፍት ፡- ( ♩ ) አንድ ምት ድምፅ አልባ መጫወትን የሚወክል ነው::**

## የተግባር ልምምድ -4

1. ከታች ያለውን የቀስት ምስል በመከተል እጃችሁን በእርጋታ እና በእኩል የጊዜ ቆይታ በማወዛወዝ የእረፍት ምልክቱን በትክክል መቁጠር ተለማመዱ::




**ጠቃሚ መረጃ ፤-**

የሩብ ፣ ግማሽ እና ሙሉ እረፍት ድምፅ አልባ ምልክቶች ዋጋ ከሩብ፣ ግማሽ እና ሙሉ ኖታ ባለ ድምፅ ምልክቶች ጋር እኩል የጊዜ ቆይታ (አቆጣጠር) አላቸው:: በዋነኝነት የኖታ እና የእረፍት ምልክቶች አቆጣጠር የሚለዩት የኖታ ምልክቶቹ በድምፅ የሚቆጠሩ ሲሆን የእረፍት ምልክቶቹ ደግሞ ድምፅ አልባ (በዝምታ) የሚቆጠሩ ናቸው::

**የእረፍት ምልክቶች በሙዚቃ ውስጥ**

- ☆ እንደ ኖታ (ባለ ድምፅ ምልክቶች) ሁሉ የእረፍት (ድምፅ አልባ) ምልክቶች በሙዚቃ ውስጥ እጅግ አስፈላጊ እና እጅግ ጠቃሚ ምልክቶች ናቸው::
- ☆ የእረፍት ምልክቶች የጊዜ ቆይታና የእረፍት ምልክቶች ስም ቀደም ሲል ከተመለከትናቸው የኖታ ምልክቶች የጊዜ ቆይታ ጋር ተመሳሳይ ናቸው::

የእረፍት ምልክቶች የጊዜ ቆይታና የኖታ ምልክቶች የጊዜ ቆይታ ወይም ጥቅም ስላየን አሁን ደግሞ የኖታ ምልክቶችን የእረፍት ምልክቶች አቆጣጠር ዘዴ በመጠቀም ተለማመዱ::

## የተግባርመልመጃ -5


1. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን ሩብ እረፍት ድምፅ አልባ ምልክቶችን በመቁጠር ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው::



2. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን ሩብ ኖታ ባለ ድምፅ ምልክቶችን ቁጠሩ::




3. ከዚህ በታች የተፃፉትን ሁለት ባለ ሙሉ ኖታ የድመፅ ምልክት ትክክለኛውን የጊዜ ቆይታቸውን (ዋጋቸውን) በመስጠት እንብቡ (ቁጠሩ)::



4. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን ሁለት ባለ ሙሉ እረፍት (ድምፅ አልባ) ምልክቶችን አንብቡ (ቁጠሩ)::



5. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን ሁለት ባለ ግማሽ ኖታ (ባለ ድምፅ) ምልክቶችን እንብቡ (ቁጠሩ)::



6. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን ሁለት ባለ ግማሽ እረፍት (ድምፅ አልባ) ምልክቶችን እንብቡ (ቁጠሩ)::



7. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን ሁለት ባለ ሩብ እረፍት (ድምፅ አልባ) ምልክቶችን እንዲቆጥሩ ያድርጉ::



8. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን ሁለት ባለ ሩብ ኖታ (ባለ ድምፅ) ምልክቶችን ቁጠሩ።



## 1.2. መሰረታዊ ቀለማት

### መግቢያ

በዚህ ክፍል ደረጃ ተማሪዎች ስለ አካባቢው የበለጠ እውቀት አድማሳቸውን የሚያሰፉበትና በተፈጥሮአዊና ማህበረሰባዊ ያሉ መስተጋብሮችን የሚከታተሉበት ሥነ-ጥበባዊ ምልከታቸውን የሚያዳብሩበትና ዕውቀትን የሚገበዩበት መንገድ ነው።

በዚህ ትምህርት ውስጥ የሦስተኛ ክፍል ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ ተፈጥሮዎችን ማለትም ወንዞች ፣ መስኮች ፣ ተራሮች ፣ ዕጽዋትና ፣ ደኖች ፣ አራዊትና አእዋፋት እንዲሁም በማህበረሰቡ በየበዓላት ጊዜ የሚለበሱ አልባሳት በቀለማት ፣ ያሸበረቁ መሆናቸውን በመረዳት ስለ ቀለማት ያላቸው ግንዛቤ ሰፋ ያለ ይሆናል።

**ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

- መስራች ቀለማትን መለየት
- መስራች ቀለማትን በስማቸው መጥራት
- በአካባቢያቸው የሚገኙ ተፈጥሮአዊና ሰውሰራሽ ቀለም ዓይነቶችን መዘርዘር

### ማነቃቂያ ጥያቄ

1. መሰረታዊ ቀለማት ስንል ፣ እነማን እና ምን ዓይነት ናቸው?


**ጠቃሚ መረጃ**

ከሥነ-ጥበብ ወይም ከእይታ ጥበብ አላባዊያን ማለትም መስመር፣ ዝርግ የሆኑ ባለሁለት

አውታረ መጠን ቅርጾች፣ ሙሉ የሆኑ ባለ ሦስት አውታረ መጠን ቅርጾች፣ የልስላሴና ሸካራነት መግለጫ ከሆነው (ቴክስቼር)፣ የቀለማት ብርሃንና ጥላ መለኪያ (ቫልዩ) እና ቀለም ናቸው፡፡ መሥራች ቀለማት በተፈጥሮ ራሰቸውን ችለው ያሉና ከሌሎች ቀለማት ጋር ተቀላቅለው የማይፈጠሩና እንዲሁም ለሌሎች ቀለማት መፈጠር ምክንያት ናቸው፡፡ በመሆኑም እርስ በራሳቸው ወይም አንዱ ከሌላው ጋር ተቀላቅለው የሁለተኛና የሦስተኛ ደረጃ ቀለማት የመፈጠር ምክንያት ናቸው፡፡

**እነሱም፡-**

- ቢጫ
- ቀይ
- ሰማያዊ



ምስል 1.1፡ የመሥራች ቀለማት

## መልመጃ -2

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ**

1. ተመሪዎች መሥራች ቀለማት ስንት ናችው?
2. የመስራች ቀለማትን ስማቸውን ዘርዝሩ?


## ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት

መስራች ቀለማት እርስ በርሳቸው ወይንም አንዱ ከሌላው ጋር ሲቀላቀል ሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን ይመሰርታሉ፡፡

- ሰማያዊ ቀለም ከቢጫ ቀለም ጋር ሲቀላቀል የሚገኘው ውጤት አረንጓዴ ቀለም ይሆናል፡፡
- ቀይ ቀለም ከቢጫ ቀለም ጋር ሲቀላቀል የሚገኘው ውጤት ብርቱካናማ ቀለም ይሆናል፡፡
- ሰማያዊ ቀለም ከቀይ ቀለም ጋር ሲቀላቀል የሚገኘው ውጤት ወይንጠጅ ቀለም ይሆናል፡፡

**እነሱም፡-**

- አረንጓዴ
- ብርቱካናማ
- ወይንጠጅ



ምስል 1.2: አንደኛ ደረጃ ቀለማት እርስበራሳቸው ሲቀላቀሉ ሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን የሚገልጽ ቻርት




ምስል 1.3: የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ቀለማት ቻርት

## መልመጃ -3

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡-**

1. ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት የምንላቸውን በስማቸው ገለጹ?
2. ሰማዊ ቀለም ከቀይ ቀለም ጋር ሲቀላቀል ምን ዓይነት ቀለም ይሰጣል?

## ሦስተኛ ደረጃ ቀለማት

☆ መስራች ቀለማት ከሁለተኛ ደረጃ ቀለማት ጋር ሲቀላቀሉ ሦስተኛ ደረጃ ቀለማትን ይሰጣሉ፡፡

**ለምሳሌ፡-**


☆ ቀይ ቀለም ከብርቱካናማ ቀለም ጋር ሲቀላቀል የሚገኘው ውጤት ቀላ ያለ ብርቱካናማ ቀለም ይሆናል፡፡

- ቢጫ ቀለም ከአረንጓዴ ቀለም ጋር ሲቀላቀል የሚገኘው ውጤት ቢጫማ አረንጓዴ ቀለም ይሆናል፡፡
- ሰማያዊ ቀለም ከ አረንጓዴ ቀለም ጋር ሲቀላቀል የሚገኘው ውጤት ሰማያዊ አረንጓዴ ቀለም ይሆናል፡፡
- ቀይ ቀለም ከወይንጠጅ ቀለም ጋር ሲቀላቀል የሚገኘው ውጤት ቀላ ያለ ወይንጠጅ ቀለም ይሆናል፡፡
- ቢጫ ቀለም ብርቱኳንማ ቀለም ጋር ሲቀላቀል የሚገኘው ውጤት ቢጫማ ብርቱኳንማ ቀለም ይሆናል፡፡
- ሰማያዊ ቀለም ከወይንጠጅ ቀለም ጋር ሲቀላቀል የሚገኘው ውጤት ሰማያዊ ወይንጠጅ ቀለም ይሆናል፡፡

**ለምሳሌ፡-**

- ቀላ ያለ ብርቱካናማ ቀለም
- ቢጫማ አረንጓዴ ቀለም
- ሰማያዊ አረንጓዴ ቀለም
- ቀላ ያለ ወይንጠጅ ቀለም
- ቢጫ ብርቱካናማ ቀለም
- ሰማያዊ ወይንጠጅ ቀለም

## የሦስተኛ ደረጃ ቀለማት ቻርት



ምስል 1.4: የሦስተኛ ደረጃ ቀለማት ቻርት

## መልመጃ -4

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡-**

1. የሦስተኛ ደረጃ ቀለማት ዓይነቶችን በስማቸው ዘርዝሩ
2. የሦስተኛ ደረጃ ቀለማት የስንተኛ ደረጃ ቀለማት ውጤቶች ናቸው?

# 1.3. ቀለል ያለ ግለ-ተውኔት እንዲሁም ፎቶ ማንሳትና የዳንስ ስነ-ምግባር

## መግቢያ

የሦስተኛ ክፍል ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚያዩዋቸው እና የሚወዷቸውን እንዲሁም የሚያደቁትን ተፈጥሯዊ እና ባህላዊ የማህበረሰብ ድርጊቶችን ማለትም ሀዘንና ደስታን የሚገልጹበት ክንዋኔዎችን ቀርጸው (ፎቶ አንስተው) በማስታወሻነት ማስቀመጥ እንዲችሉ ከእይታዊ ጥበብ አንዱ የሆነውን በቀላሉ ፎቶ የማንሳት ዘዴን በመለማመድ ክህሎታቸውን ለማዳበር ይረዳል፡፡

## ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኂላ የሚጠበቅባቸው፡-

- በቀላሉ ፎቶ የማንሳት ዘደ ምንነት መለየት
- ቀላል የፎቶ ማንሻ ምሳሪያዎችን ማነጻጸር
- ቀላል የፎቶ ማንሻ መሳሪያዎችን ማየት
- ፎቶ የማንሳት ጠቀሜታን መናገር
- ተማሪዎች የድራማን ምንነትን ይረዳሉ፡፡
- ተማሪዎች በድራማ ዉስጥ የሚገኙ ነጥቦችን አዝናኝና አሳዛኝ የድራማ (ተዉኔት) ዓይነቶችን ይረዳሉ፡፡

## ማንቂያ( መሪ ተግባራት)

1. ቀላል ፎቶ የማንሳት ዘዴ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ፎቶ ማንሳት ያለውን ጥቅምና ፋይዳ ዘርዝሩ፡፡

### 1.3.1. በቀላሉ ፎቶ የማንሳት ዘዴ

## ጠቃሚ መረጃ


በቀላሉ ፎቶ የማነሳት ጥበብ ስንል የሦተኛ ክፍል ተማሪዎቸ በአካባቢያው በቅርበት ከወላጆቻቸው ፎቶ ማንሻ ያላቸውን የእጅ ስልኮችን በመጠቀም በቤታቸው አካባቢ የሚገኙትን አበባዎችን፣ የቤተሰብ አባላትን፣ የቤት

አንስሳቶችን፣ ቁሳቁሶችን፣ ዛፎችን፣ ተራራዎችን ወዘተ... ማንሳት በቀላሉ ሊለማመዱ ይችላሉ፡፡

**ለምሳሌ፡-** ከአበባ ዓይነቶች አደይ አበባ፣ ጽገረዳ፣ የመስቀል አበባ (እንግጫ) ለሎችም ወዘተ...



ምስል 1.5፡ ከአበባ ዓይነቶች ጥቂቶቹ




ምስል 1.6፡ ቤት እንስሳትን የሚገልጹ ስዕሎች



ምስል 1.7፡ ህጻናት በቀላሉ ፎቶ ማነሳት ሚለማመዱባቸው የአበባ ዓይነቶች ወይም ፎቶ



ምስል 1.8: የቤት ውስጥ መገልያ ቁሳቁሶች የሚገልጹ ስዕሎች



ምስል 1.9: የዛፎችና ተራራዎችን ማሳየት ወይም መግለጽ የሚችሉ ስዕሎች

## መለመጃ -5

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡-**

1. ፎቶ ማንሻ ቁሳቁሶች ምን ተብለው ይጠራሉ?
2. የፎቶ ማንሻ ጥቅሞችን በቡድን ተወያይታችሁ በጽሁፍ አቅርቡ?

## የማነቃቂያ ጥያቄ

1. ተማሪዎች ድራማ ማለት ምን ማለት ነዉ?
2. ተማሪዎች አዝናኝና አሳዛኝ ድራማ ምንድን ናቸዉ?

## 1.3.2. ድራማ

ድራማ ከትውን ጥበባት ዘርፎች ውስጥ የሚካተት ነው፡፡ ድራማ የሰው ልጆችን የእለት ከእለት ገጠመኝ አስመስሎ ታሪክን መነሻ በማድረግ የሚከወን ድርጊት ነው፡፡ የድራማ ታሪክ ታሪክ የምንለው መነሻ ሃሳብ ፣ መካከለኛ ሃሳብ እና ማጠቃለያ ሃሳብ ያለው ሲሆን ታሪክ ከጊዜ አኳያ ድርጊቶች በቅደም ተከተል ተንትነው የሚቀመጡበት ክፍል ነው፡፡

**ድራማ ምንድን ነው?**

ድራማ የሚለው ቃል የመጣው ማድረግ ፣ መሥራት ፣ መከወን ፣ ከሚለው ቃል ሲሆን ድራማ ከመባሉ በፊት ጨዋታ በመባል ይታወቅ ነበር፡፡ ጨዋታ የሚለው ቃል ለበርካታ ዘመናት ድረስ ለድራማዎች መደበኛ ቃል ሆኖ ያገለግል ነበር፡፡ ይህም ከድራማ ተዋናይ ይልቅ ሠሪ እና ማሳያ ሕንፃው ከቲያትር ቤት ይልቅ የመጫወቻ ቤት ይባል ነበር፡፡

ድራማ ማለት በቲያትር ውስጥ፣በሬዲዮ፣በቴሌቪዥን የተከናወነ ጨዋታ ፣ ኦፔራ ፣ ማይም እና ወ.ዘ.ተ. የሚያካትት ሲሆን ክንዋኔዎች ወይም ድርጊቶች በሙሉ ድራማዎች ናቸው፡፡ ማመንን ፣ ማስመሰልን ፣ በመተግበር ማስተላለፍን ያካትታል፡፡

ከድራማ ጋር የተቆራኙት ሁለቱ ጭምብሎች ማለትም አዝናኝ እና አሳዛኝ ክስተቶች ድራማውን ይወክላሉ፡፡ ተውኔቶች ሙሉ በሙሉ አሳዛኝ ወይም አስቂኝ አይደሉም ነገርግን የሁለቱም ቅጾች ለማካተት ያቀናብራሉ፡፡ ይህ ተመሳሳይ መሠረታዊ ቅርፅ ባላቸው የተለያዩ ተውኔቶች መካከል እንዲለዩ ይረዳቸዋል፡፡

**አሳዛኝ እና አዝናኝ**



**አሳዛኝ (ትራጄዲ)**

ከጥንት ዘመናት ጀምሮ አሳዛኝ ደራማ በጣም የታወቀ የድራማ ዓይነት ነው:: እሱም ከባድ እርምጃን ለማሳየት እና በጨዋታው ውስጥ ከባድ ድርጊቶችን ይይዛል:: በአሰቃቂ ሁኔታ ውስጥ አስቂኝ እፎይታዎች ሊኖሩ ይችላሉ:: አሳዛኝ ተውኔቶች ስለ ሰው ሕልውና ተፈጥሮ ፣ ስለ ሥነ ምግባር ወይም ስለ ሰብዓዊ ግንኙነቶች ጉልህ ጉዳዮችን ያነሳሉ:: በጨዋታው ውስጥ ያለው ዋና ገጸ-ባህሪን ተከትለው ብዙውን ጊዜ ተመልካች የገጸ-ባህሪው ስሜት ዉስጥ እንዲገቡ እንዲራሩ የሚያደርግ ሰው ነው:: በተለምዶ ባለታሪኩ ጥሩ ወይም ክቡር የሆነ ነገር ለማሳካት ሊሞክር ይችላል:: አሳዛኝ ድራማ የተለያዩ አሳዛኝ ክስተቶችን እያስተናገደ በአሰቃቂ ሁኔታዎች የተሞላ ተውኔት ነው::

**አዝናኝ (ኮሜዲ)**

አሳዛኝ የሰው ልጅ በምድር ላይ ስለመኖራቸው ትልቅ ጥያቄዎች ቢሆንም ፣ ምን ያህል የማይረባ ሕይወት ሊኖር እንደሚችል ያሳያል:: ይህ አስደናቂ ቅርፅ እንዲሁ መነሻው በጥንታዊ ግሪክ ውስጥ ነው:: አስቂኝ ብዙውን ጊዜ የሚከሰተው ከተለመደው ወይም ከተጠበቀው ድርጊት አንዳንድ ዓይነት የተለዩ የሚያስቁ ክስተቶች የሚታይበት ነው:: እንዲሁም አንድ ገጸ-ባህሪ በሚያስገርም ወይም ባልተጠበ ሁኔታ ሊከውን ይችላል:: ኮሜዲ ብዙውን ጊዜ እያዝናና የምያስተምር ነው:: በዋናነት ማዝናናት እና በማሳቅ ክስተቶች ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት:: ብዙውን ጊዜ ድርጊቱ ሁሉም የሚተወነው በአዝናኝ ሁኔታ ውስጥ ነው:: ለምሳሌ በሙዝ ልጣጭ ላይ በሚንሸራተት ሰው ላይ መሳቅ ቀላል ነው ፣ ግን ግለሰቡ ጀርባውን እንደተሰበረ ካወቅን ፣ በጣም አስቂኝ መሆኑ ያቆማል:: የኮሜዲ የመጨረሻው ዓላማ አድማጮች ወደ አዝናኝ ጨዋታው እንዲገቡ መጋበዝ እና በመድረክ ላይ ካሉ ገጸ-ባህሪዎች ጋር ወይም በሳቅ መሳተፍ ነው::

## መልመጃ -6

1. ድራማ ምንድን ነው?
2. ድራማ በስንት ይከፈላል ምን ምን ናቸው?
3. አሳዛኝ ድራማ ምንድን ነው?

4. አዝናኝ ድራማ ምንድን ነው?

## የዉዝዋዜ ሥነ-ምግባር

ዉዝዋዜ በተመልካች ፊት ለፊት ወይም በካሜራ ፊት የሚከወን ትዉን ጥበብ ነው። ውዝዋዜ የተከበረ ሙያ ነው። ዉዝዋዜ ድግግሞሽ ወይም ልምምድ የፈልጋል። በዚህ ድግግሞሽ ወቅት ትዕግስትና ስነምግባር ያስፈልጋል። ሌሎች አብረዉን የሚሰሩ አጋሮቻችን ተወዛዋዦችን ማክበር ያስፈልጋል። የምንሠራውን ውዝዋዜ ለይተን ማወቅ ለስራችን ክብር መስጠትን ያሳያል። ውዝዋዜ በሚፈለገው የዝግጅት ልክ መዘጋጀት አለበት። ባህላዊ ውዝዋዜ የምንሠራ ከሆነ የባህሉ ባለቤት አለባበስን ማሳየት ያስፈልጋል ። ለምሳሌ፡- የጉራጌ ብሔረሰብ ባህልን የምናሳይ ከሆነ የብሔረሰቡን አልባሳት ማዘጋጀት ያስፈልጋል። በጠቅላላው ተወዛዋዦች የውዝዋዜን ሥነ-ምግባር አጥብቀው የሚከተሉ መሆን አለባቸው።

## ሙከራ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ**

ሀ. ተወዛዋዥ ምግባረ ሰናይ መሆን አለበት።

እውነት/ሐሰት

ለ. ውዝዋዜ የተከበረ ሙያ ስለሆነ ተወዛዋዥ ሌሎችን ማክበር የለበትም።

እውነት/ሐሰት

ሐ. ተወዛዋዥ የውዝዋዜ ዝግጅት አያስፈልገውም።

እውነት/ሐሰት

መ. ተወዛዋዥ ለሌሎች አረአያ መሆን አለበት።

እውነት/ሐሰት

## የምዕራፍ ማጠቃለያ

በአንድ የንግግር ቋንቋ ውስጥ ያሉ የንግግር ድምፆችን ለመፃፍ ፊደላትን እንደምንጠቀመው ሁሉ በሙዚቃ ውስጥ የምናገኛቸውን ድምፆች ለመፃፍ የምንጠቀምበት ዘዴ ደግሞ ኖታ /የኖታ ዘዴ/ በመባል ይታወቃል፡፡

ሙዚቃ ቋንቋ ነው የምንለውም እንደማንኛውም ቋንቋ የሚፃፍ፣ የሚነበብ፣ የሚደመጥ የራሱ ፊደላት (ኖታዎች)ያሉት በመሆኑ ነው፡፡

በምንኖርባት ዓለም ውስጥ ያሉ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ የራሳቸው ሙዚቃ አላቸው፡፡ ይህም ማለት ያለ ሙዚቃ የሚኖር ማህበረሰብ በምድራችን ውስጥ የለም ማለት ነው፡፡ ሙዚቃ ሰዎች አስተሳሰባቸውን ፣ ፍላጎታቸውን፣ አኗኗራቸውን ፣ ሃዘናቸውን ፣ ደስታቸውን ወ.ዘ.ተ. ከሚገልፁባቸው መንገዶች ውስጥ አንደኛው የጥበብ ውጤት ሙዚቃ ነው፡፡

የሙዚቃ ኖታ ምልክቶች በሙዚቃ ውስጥ የሚሰጡት ግልጋሎት ከፍተኛ ነው፡፡ እነዚህ የኖታ ምልክቶች በሙዚቃ ውስጥ የምናገኘውን እያንዳንዱን ድምፅ በምን ያህል የጊዜ ቆይታ መጫወት እንዳለብን ወይም የድምፁን የጊዜ እርዝመት መጠን የምንለካባቸው ናቸው፡፡ የኖታ ምልክቶች ድምፅን የሚወክሉልን ሲሆን በተቃራኒው የእረፍት ምልክት የምንላቸው ደግሞ ድምፅ-አልባ /ዝምታን/ የሚወክሉ ናቸው፡፡

በሙዚቃ ውስጥ ያለውን የድምፅ ቆይታ የሚወክሉ በርካታ የሙዚቃ ኖታ ምልክቶችን በሙዚቃ ውስጥ እናገኛለን፡፡

## የማጠቃለያ ጥያቄዎች

**መመሪያ 1 ከዚህ በታች ለተዘረዘሩ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ**

1. በሙዚቃ ውስጥ ኖታ የምንለው /የኖታ ምልክት/ ምንን ይወክልልናል?
2. በሙዚቃ ውስጥ እረፍት የምንለው /የእረፍት ምልክት/ ምንን ይወክልልናል?

3. በሙዚቃ ውስጥ የምናገኛቸውን ድምፆች ለመፃፍ የምንጠቀምበት ዘዴ ምን በመባል ይታወቃል?
4. በሙዚቃ ውስጥ ሙሉ ኖታ ስንት ምቶች /የጊዜ ቆይታዎች/ አሉት?
5. በሙዚቃ ውስጥ ግማሽ ኖታ ስንት ምቶች /የጊዜ ቆይታዎች/ አሉት?
6. በሙዚቃ ውስጥ ሩብ ኖታ ስንት ምቶች /የጊዜ ቆይታዎች/ አሉት?
7. በሙዚቃ ውስጥ ሙሉ እረፍት ስንት ምቶች /የጊዜ ቆይታዎች/ አሉት?
8. በሙዚቃ ውስጥ ሩብ እረፍት ስንት ምቶች /የጊዜ ቆይታዎች/ አሉት?
9. በሙዚቃ ውስጥ ግማሽ እረፍት ስንት ምቶች /የጊዜ ቆይታዎች/ አሉት?
10. ግማሽ ኖታ እና ሩብ ኖታ ስንት አይነት አፃፃፍ አላቸው?

**መመሪያ 2 ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ**

1. ከሚከተሉት መስራች ቀለም ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ/ወይንጠጅ

   ለ/ቢጫ

   ሐ/ሰማያዊ

   መ/ቀይ

2. ከቤታችን በቀላሉ ፎቶ ለማንሳት የምንችላቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?

   ሀ/ የቤትውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች

   ለ/የቤትእንስሳት

   ሐ/የወላጆቻችንን

   መ/ሁሉም

3. ከሚከተሉት ውስጥ ሁለተኛ ደረጃ ቀለም የቱ ነው?

   ሀ/ቀይ

   ለ/ ሰማያዊ

   ሐ/ብርቱካናማ

   መ/ቢጫ

4. ሦስተኛ ደረጃ ቀለማት ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ/ ቀላ ያለ ብርቱካናማ

   ለ/ ቀይ

   ሐ/ ቢጫማ አረንጓዴ

   መ/ ሰማያዊ ወይንጠጅ

5. ለቀለሞች መቀላቀያ የማያገለግል ቁስ የቱ ነው?

   ሀ/ ወንፊት

   ለ/ ዝርግ ሳህን

   ሐ/ ቀለም መቀቢያ(ብሩሽ)

   መ/ ውሃ

**መመሪያ 3 የሚከተሉት ጥያቄዎችን እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ**

1. ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት በተፈጥሮ ራሳቸውን ችለው ያሉ ቀለማት ናቸው፡፡
2. ቢጫ ቀለም ከሰማያዊ ቀለም ጋር ሲቀላቀል ብርቱካናማ ቀለም ይሰጣል፡፡
3. የእጅ ስልኮች ቀላል ፎቶ ማንሻ ሆነው ማገልገል ይችላሉ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. የተግባር ልምምድ

### መግቢያ

በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ የሦስተኛ ክፍል ተማሪዎች የእይታ ጥበብንና ሥነ-ዉበትን መግለጽ ከሚያስችላቸው እና እውቀት የሚያገኙበት አንዱና ዋነኛው መንገድ የተግባር ልምምድ ነው፡፡ የተግባር ልምምድ ተማሪዎች ማንኛውንም የጽንሰ ሀሳብ ትምህርቶች ወደ ተግባር ልምምድ ማድረግ የሚያስችላቸው የተመቻቸ ጊዜ እና አመቺ ቦታ ሊኖር ይገባል፡፡ ይህ የተግባር ልምምድ ተማሪዎች አካባቢያቸው ከሚገኙ ተፈጥሯዊ እና ሰው ሠራሽ ቁሶች (ግብዓቶች) የራሳቸውን ፈጠራዊ ገለጻዎችን ለማዳበር ያስቸላቸዋል፡፡

**ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

- የኖታ ምልክቶችን (ጊዜ እና የእረፍት ምልክቶችን የማንበብ እና የመፃፍ ልምምድ ያደረጋሉ፡፡
- በድምፅ ከማንበብ በተጨማሪ የምት ሙዚቃ መሳሪዎችን በመጠቀም ኖታዎችን ያነባሉ፡፡
- በሙዚቃ ፣ በውዝዋዜ እና በማስመሰል ትውን ጥበባት አርአያ / ምሳሌ/ የሚሆን ቤተሰብ የሚያደረጋቸውን ተግባራት እንዲያቀርቡ ማደረግ፡፡
- መሳል ፣ መንደፍ ፣ ቀለማትን መቀላቀል ማተም እና ማቅለም

## 2.1. ድምፅ፣ ሙዚቃ፣ ኖታዎች እና የምት ሙዚቃ መሳሪያዎች

### መግቢያ

ሙዚቃ ማለት ድምፆችን በማዋቀር (በማቀናጀት) ለጆሮ በሚስብ እና በሚማርክ መልኩ ሀሳባችንን እና ስሜታችንን የምንገልፅበት አንደኛው የጥበብ መንገድ መሆኑ በክፍል አንድ ትምህርታችን ላይ ገልፀን ነበር፡፡

ይህንን ስንል አንድን ሙዚቃ ለመስራት በዋነኝነት ከሚያስፈልጉ ነገሮች አንደኛው ድምፅ ነው፡፡ በዚህ ምእራፍ ውስጥም ድምፅ በሙዚቃ ውስጥ ያለውን ሚና እና ድምፅ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንማራለን፡፡

**ከዚህ ምእራፍ በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

- በሙዚቃ ውስጥ ድምፅ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይረዳሉ፡፡
- ስንት አይነት የድምፅ አይነቶች እንዳሉ ይለያሉ፡፡
- የምት የሙዚቃ መሳሪያዎችን አሰራር ይረዳሉ
- በአካባቢያቸው ያሉ ቁሳቁሶችን በመጠቀም የምት የሙዚቃ መሳሪያዎችን በቡድን በመሆን ይሰራሉ፡፡
- በአካባቢያቸው ያሉ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች ምን ምን እንደሆኑ ያወቃሉ፡፡
- በምት የሙዚቃ መሳሪያዎች ኖታዎችን ያነባሉ፡፡

### የማነቃቂያ ጥያቄ

1. ድምፅ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ድምፅ እንዴት ይፈጠራል?

### 2.1.1. ድምፅ

ድምፅ ማለት ማንኛውም ነገር (ቁስ) በሚርገበገብበት ወይም እርስ በእርስ በሚጋጭበት ጊዜ የሚፈጠር በጆሮ ልንሰማው የምንችለው ነገር ሁሉ ድምፅ ይባላል፡፡

## ሀ. የድምፅ አፈጣጠር

ድምፅ ማለት ማንኛውም ነገር (ቁስ) በሚረገበገብበት ወይም እርስ በእርስ በሚጋጭበት ጊዜ የሚፈጠር በጆሮ ልንሰማው የምንችለው ነገር እንደሆነ ከላይ በመግቢያችን ገልፀን ነበር፡፡ በእርግብግቢት የሚፈጠሩ ድምፆች ተርገብጋቢው ነገር (ቁስ) አየሩን በሚቀዝፍበት ጊዜ የሚፈጠር ድምፅ ሲሆን ይህም ረዘም ላለ ጊዜ ወይንም እርግብግብታው እስኪቆም ድረስ ድምፁን ልንሰማው እንችላለን፡፡

**ለምሳሌ** የተወጠረ የክራርን ገመድ (ሲር) ስበን ስንለቀው ገመዱ ወዲያውኑ ድምፅ ይፈጥርልናል፡፡ የድምፅ ቆይታውም የገመዱ ርግብግብታ እስከሚያቆም ድረስ ልንሰማው እንችላለን፡፡

### ከንዑስ ክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች


- ድምጽ ማለት ምን እንደሆነ እንዲያውቁ ማድረግ
- ድምጽ እንዴት እንደሚፈጠር ይረዳሉ
- ድምጽ የሚፈጥሩ መሳሪያዎችን በአካባቢቸው ከወዳደቁ ቁሶች እንዲሰሩ ማድረግ፡፡

በማጋጨት እና በማፋጨት የሚፈጠሩ ድምፆች በአብዛኛው ጊዜ የድምፅ ቆይታቸው የሚወሰነው እንደ መሳሪያዎቹ (እንደሚጋጩት ነገሮች) የመርገብገብ ባህሪ ነው፡፡ ተማሪዎች አካባቢያቸው ላይ ባሉ ነገሮች እንዲማሩ ማደረግ ተገቢ ነው፡፡

ይህ ማለት ለምሳሌ በእስክርቢቷችሁ የተቀመጣችሁበትን ወንበር ወይም ጠረጴዛ ብትመቱ ወድያውኑ ድምፅ ሲፈጠር ትሰማላችሁ፡፡ ነገር ግን በእስክርቢቷችሁ የመታችሁት ጠረጴዛ ወይም ወንበር የተሰራው ከእንጨት ከሆነ የድምፅ ቆይታው በጣም አጭር ጊዜ ብቻ ሲሆን በአንፃሩ ከብረት (ቆርቆሮ) ከሆነ ደግሞ የድምፅ ቆይታው ከቀድሞው ሊረዝም ይችላል፡፡ ሌላው መጠኑ ከፍ ባለ የቀለም ቆርቆሮ ወይም ውስጡ ክፍት በሆነ ገበታ መሰል ነገር ላይ ቆዳ ወጥረን በዱላ ብንመታው ድምፁን ረዘም ላለ የጊዜ ቆይታ ልንሰማው እንችላለን፡፡ ይህም ሚሆነው የቀለም ቆርቆሮው ወይም ገበታው ውስጡ ክፍት በመሆኑ የቆዳውን እርግብግብታ ይዞ ስለሚቆይ ነው፡፡



ምስል 2.1: ሾንካ




Generated by CamScanner from intsig.com


ምስል 2.2: ክራር

## የተግባር መልመጃ 1

1. ልጆች በአካባቢያችሁ የወዳደቁ ጣውላዎችን እና ጅማት (ሲር) በመጠቀም ክራር አዘጋጅታችሁ ከጅማቱ ድምፅ እንዴት እንደሚወጣ ለማየት ሞክሩ።

## የተግባር መልመጃ -2

1. መምህራችሁ በሚያሳዩአችሁ መሰረት በአካባቢያችሁ የሚገኙ ቁሶችን በመጠቀም ከበሮ ወይም አታሞ መስራትን ተለማመዱ።



ምስል 2.3: ቲምባ



ምስል 2.4: ነጋሪት



ምስል 2.5: አታሞ

## ለ. የድምፅ አይነቶች

በቀደመው ትምህረታችን ድምፆች እንዴት እንደሚፈጠሩ አይተናል በመቀጠል ደግሞ የድምፅ አይነቶች ስንት እንደሆኑ እና ምን አይነት ባህሪ እንዳላቸው እናያለን፡፡

ድምፆች ባላቸው ባህሪያት መደበኛ (ሙዚቃዊ) እና መደበኛ ያልሆኑ (ኢ-ሙዚቃዊ) ብለን በሁለት እንከፍላቸዋለን፡፡

### 1. ሙዚቃዊ (መደበኛ) ድምፆች

መደበኛ (ሙዚቃዊ) ድምፆች የምንላቸው ውስን በሆነ የድምፅ እርግብግብታ የሚፈጠሩ እና ለጆሮ የማይረብሹ ወይም የሚመቹ ሙዚቃዊ ድምፆች ሲሆኑ እነዚህንም ድምፆች በአካባቢያችንም ሆነ በአለማችን ለሙዚቃ ስራ ምንጠቀምባቸው ናቸው፡፡

በአብዛኛው የአለማችን ሙዚቀኞች የሚጠቀሙበት የሙዚቃ መሳሪያም እነዚህን መደበኛ ሙዚቃዊ ድምፆች የሚያወጡ ወይም በእነዚህ ድምፆች የተቃኙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የፒያኖ /ኪቦርድ/ ቁልፎችን በመጫን የምንሰማቸው ድምፆች መደበኛ የሆኑ እና የራሳቸው ስሞች ያሏቸው ናቸው፡፡

### 2. ሙዚቃዊ ያልሆኑ (ኢ-መደበኛ) ድምፆች

መደበኛ ያልሆኑ (ኢ-ሙዚቃዊ) ድምፆች የምንላቸው ደግሞ ባልተወሰነ በሆነ የድምፅ እርግብግብታ የሚፈጠሩ እና ለጆሮ የሚሰቀጥጡ ሸካራ ድምፆች ሲሆኑ የሚረብሹና የሚያውኩ ድምፆች ናቸው፡፡

ለምሳሌ ያህል በገበያ አካባቢ የምንሰማቸው ሁካታዎች ፣ ከመጠን በላይ ጮክ ብሎ የሚሰማ ሙዚቃ ፣ የትራፊክ መጨናነቅ በሚበዛበት አካባቢ የሚሰሙ የመኪና ጥሩንባዎች ወ.ዘ.ተ… ሲሆኑ። እነዚህ አይነት ድምፆች አዕምሮን የሚረብሹ እና ጤናንም የሚጎዱ ድምፆች ናቸው።

## መልመጃ -1

1. ድምፅ እንዴት ይፈጠራል?
2. ስንት አይነት ድምፆች አሉ?
3. ሙዚቃዊ /መደበኛ/ ድምጽ የምንላቸው ምን አይነት ድምፆችን ነው?
4. 4. ኢ-ሙዚቃዊ /ኢ-መደበኛ/ ድምጽ የምንላቸው ምን አይነት ድምፆችን ነው?

## 2.1.2. የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች

የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች የምንላቸው የተወጠሩ ቆዳዎችን በምንመታበት ጊዜ ድምፅ የሚፈጥሩ የሙዚቃ መሳሪያዎች ሲሆኑ እነዚህንም አይነት የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች በተለያዩ የሃገራችን ክፍሎች እናገኛቸዋለን። ቲምባ ፣ ከበሮ ፣ አታሞ ፣ ድቤ ፣ ነጋሪት ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት በሃገራችን ከሚገኙ የምት የሙዚቃ መሳሪዎች ውስጥ የሚካተቱ ናቸው።

ኢትዮጵያ ለሰው ልጅ መገኛ ብቻ ሳይሆን  ለሙዚቃ ፣ ዘፈኖች ፣ ኪነጥበብ እና የባህል አገር በቀል እውቀቶች ባለቤት ናት።

ኢትዮጵያ በመላው አፍሪካ አህጉር ውስጥ ልዩ የባህል ቅርስ እና የተለያየ የሙዚቃ ታሪክን አገር በቀል እውቀቶች ጠብቃ አስቀጥላለች። በአገራች ውስጥ የተለያዩ ብሔረሰቦች እንደ ማሲንቆ ፣ ክራር ፣ ዋሽንግት ፣ በገና እና ከበሮ ያሉ የራስዋ የተለየ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች አሏት።

በሰፊው እንደሚታወቀው አብዛኛዎቹ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ከእንጨት፣ ከቀርከሃ ፣ ከእንስሳት ቆዳ እንዲሁም ከእንስሳት ቀንድ ጥቂቶቹን ለመጥቀስ የተሰሩ ናቸው።

የጋሞ ሕዝቡ ከሌላው ዘመናዊና ባህላዊ መሣሪያዎች ከሌሎች የሙዚቃ ድምፆች የሚለየው ሌላ ተጨባጭ ቁሳዊ ነገር ሳይጠቀም በሰው ድምፅ ቅላፄ

ብቻ የሚዘጋጅበት ኤድዶ የሚባል ልዩ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ አለው::

ከብዙ ሌሎች የሙዚቃ መሣሪያዎች በተቃራኒ ኤድዶ ሰባት የተለያዩ ድምፆችን ወይም ማስታወሻዎችን ማለትም አይፌ፣ አይፊቃለቶ፣ ዱንቤ፣ ዱንቤካሌቶ፣ ቱቻ፣ ፊላ እና ፊላካለቾን ይመርጣል::

ለእያንዳንዱ ድምጽ ፣ በእሱ ውስጥ ልዩ ያደረጉ አንዳንድ ሰዎች አሉ:: የኤድዶ ሙዚቃ ጨዋታ በአይፌ ተጀምሯል ከዚያም ሌሎቹ ከላይ በተጠቀሱት ቅደም ተከተል መሠረት ይከተላሉ::

የጋሞ ሰዎች ለባህላዊ ሙዚቃቸው የሰውን ድምፅ እንደ መሣሪያ ይጠቀማሉ:: ነገር ግን ይህ ልዩ ባህላዊ አገር በቀል ዕውቀት ብዙ ቦታዎች እውቅና የለውም:: ከኤድዶ በተጨማሪ እንደ ሌሎች የአገሪቱ ብሔረሰቦች ሁሉ ዶርዜ እንደ ሌሎች ዛይ (የአካባቢው መለከት) ፣ ዲታ (ክራር) እና ከበሮ ካሉ ተጨባጭ ቁሳቁሶች የተሠሩ ሌሎች ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ይጠቀማሉ::

## የማንቂያ ጥያቄ:-

1. በአካቢያችሁ የሚታወቁ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ምን ምን ናቸው?
2. ለምን አይነት የሙዚቃ ስራ ትጠቀሙባቸዋላችሁ?

## ጠቃሚ መረጃዎች

**ትምባ:-** የምት የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን ከከበሮ ጋር ተመሳሳይነት አለው:: በቀደመው ዘመን ትምባ የሚዘጋጀው ቀለል ያለ እንጨት ውስጡ ተቦረቡሮ ቆዳ በመሸፈን ነበር ዛሬ ላይ በእንጨት ምትክ የገረወይና ቆርቆሮ ጥቅም ለትምባ ምቹ እንዲሆን በከርሞሃ የእደ ጥበብ ባለሙያዎች ተቀጥቅጦ ይዘጋጅና በቆዳ እና በጠፍር ይወጠራል:: ትምባ በአንዳንድ የደቡብ ኢተዮጰያ አካባቢ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች በሐዘንም ሆነ በደስታ ጊዜ ጭፈራን ለማድመቅ የሚጠቀሙበት የሙዚቃ መሳሪያ ነው::

**አታሞ:-** በጉራጌ ብሄረሰብ ውስጥ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች በብዛት የሚጠቀሙበት የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን መጠኑ አነስተኛ የሆነ እና በእጅ የሚመታ የምት የሙዚቃ መሳሪያ ነው:: አታሞ ከሸክላ (ድስት) ላይ የፍየል ወይም የበግ ቆዳን በመወጠር ሊሰራ ይችላል::



ምስል 2.6: አታሞ

**ነጋሪት፡-** የምት የሙዚቃ መሳሪዎች ከምንላቸው ውስጥ የሚካተት ሲሆን በቀድሞ ጊዜ ነገስታት አዋጅ ለማወጅ እና በጦርነት ወቅት መልዕክት ለማስተላለፍ ይጠቀሙበት ነበር፡፡ ነጋሪት ከእንጨት እና ከቆዳ የሚሰራ ሲሆን ውስጡ ከተቦረቦረ እና ገበታ ከመሰለ እንጨት ላይ ቆዳ በመወጠር የሚሰራ የምት ሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡ የምንጫወተውም አጭር እና ከወደ ቂጡ ቆልመም ባለ ዱላ በገበታው ላይ የተወጠረውን ቆዳ በመምታት ነው፡፡



ምስል 2.7: ነጋሪት


**ከበሮ፡-** የኢተዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቄሶች የሚጠቀሙበት የምት ሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን ከሌሎች የሀገራችን የምት ሙዚቃ መሳሪያወች የሚለየው መጠኑ ከፍያለ እና የሲሊንደር ቅርፅ ያለው ነው፡፡ በሁለቱም

በኩል በእጅ በመምታት ሁለት የተለያዩ ድመፆችን ማውጣት የሚችል የምት የሙዚቃ መሳሪያ በመሆኑ ነው፡፡ ከበሮ ከእንጨት፣ ከነሀስ፣ ከመዳብ እና ከብር ሊሰራ ይችላል፡፡ እንጨቱ ከተቦረቦረ እና ውስጡ ክፍት ከሆነ በኋላ በሁለቱም አቅጣጫ ቆዳ በመወጠር የሚሰራ የምት የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡ ሰፊውን የከበሮ ክፍል በቀኝ እጃችን ጠባቡን የከበሮ ክፍል ደግሞ በግራ እጃችን በመምታት ከበሮን መጫወት እንችላለን፡፡



ምስል 2.8: ከበሮ

ሃላካ፡- ሃላካ የሚባለው ባህላዊ የምት የሙዚቃ መሳሪያ እንጨቶችን በአጭሩ በመቆራረጥ እና በመጥረብ ለእጅ አያያዝ እንዲመች ተደርጎ የሚዘጋጅ የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡ ሃላካ በእጅ ከማጨብጨብ ይልቅ በሃላካ ማጨብጨብ ጨዋታን ስለሚያደምቅ ጭብጨባን የሚተካ ነው፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ሃላካ ከጭብጨባ ጋር ግንኙነት የለውም እንደ አንድ የሙዚቃ መሳሪያ ዘፈኖችን ለማጀብ የሚውልና የራሱ የዘፈኑም መጠሪያ ነው የሚሉ አሉ፡፡ በተለይም ሃላካ የተሰኘው ዜማ ማጀቢያ ሃላካ የተባለው የምት የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡



ምስል 2.9: ሃላካ (ጋይሌ)

## መልመጃ 2

1. ሃለካ የምንለው የሙዚቃ መሳሪያ ከምን ይሰራል?
2. በቀድሞ ጊዜ ነገስታት አዋጅ ለማወጅ እና በጦርነት ወቅት መልዕክት ለማስተላለፍ ይጠቀሙበት የነበር የምት የሙዚቃ መሳሪያ ምን ይባላል?
3. ከከበሮ ጋር ተመሳሳይነት ያለው የምት የሙዚቃ መሳሪያ ማን ይባላል?

## 2.1.3. በምት የሙዚቃ መሳሪያዎች ኖታዎችን ማንበብ

በባህል የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች ታግዞ ኖታዎችን ማንበብ ማለት በመጀመሪያው የትምህርታችን ምዕራፍ ላይ ያሉትን የኖታ እና እረፍት ምልክቶች ላ..ላ.. ወይም ታ..ታ.. እያልን በአፋችን እናነባቸው የነበሩትን በምት የሙዚቃ መሳሪያ ተክቶ ማንበብ ማለታችን ነው፡፡

መምህራችሁ በሚያሳዩአችሁ መሰረት ከዚህ በታች የተቀመጡትን የኖታ እና የእረፍት ምልክቶች ለማንበብ ሞክሩ





## 2.2. ቀላል የሆኑ ዝርግ ቅርጾችን ባለሁለት እና ሦስት አውታር መጠን ቅርጾችን መንደፍ እና ማቅለም

### መግቢያ

በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ የሦስተኛ ክፍል ተማሪዎች የእይታ ጥበብንና ሥነ-ውበትን መግለጽ ከሚያስችላቸው እና እውቀት የሚያገኙበት አንዱና ዋነኛው መንገድ የተግባር ልምምድ ነው፡፡ የተግባር ልምምድ ተማሪዎች

ማንኛውንም የጽንሰ ሀሳብ ትምህርቶች ወደ ተግባር ልምምድ ማድረግ የሚያስችላቸው የተመቻቸ ጊዜ እና አመቺ ቦታ ሊኖር ይገባል፡፡ ይህ የተግባር ልምምድ ተማሪዎች አካባቢያቸው ከሚገኙ ተፈጥሯዊ እና ሰው ሠራሽ ቁሶች (ግብዓቶች) የራሳቸውን ፈጠራዊ ገለጻዎችን ለማዳበር ያስቸላቸዋል፡፡

**ከዚህ ንዑስ ክ/ትምህርት በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

- ቀላል የሆኑ ዝርግ ቅርጾች ወይም ባለ ሁለት አውታረመጠን ቅርጾን ይለያሉ
- ባለ ሁለትና ባለ ሦስት አውታረመጠን ቅርጾች ልዩነት ይገልጻሉ
- ባለ ሦስት አውታረመጠን ቅርጾችን ቀለም ይቀባሉ
- የቀጥታ ህትመትን በማትም ይተገብራሉ

**ማንቂያ (መሪ ተግባራት)**


1. ተማሪዎች ባካባቢቻው ያዩዋቸውንና የሚያውቁዋቸው ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሠራሽ የቀለም ዓይነቶች በቡድን ተወያይታችሁ በዝርዝር አቅርቡ

**ጠቃሚ መረጃዎች**

ቀላል የሆኑ ባለ ሁለት አውታረ መጠን ያላቸው ዝርግ ቅርጾች ማለት በእይታዊ ጥበብ ውስጥ የሚገለጹት በውጫዊ መስመር አማካኝነት ነው፡፡ ባለ ሁለት አውታረመጠን ያላቸው ዝርግ ቅርጾች በተፈጥሯዊና በሰው ሰራሽ ቁሳቁሶችን በነጠላ መሥመር በመንደፍ የሚገለጽበት መንገድ ወይም ዘዴ ነው፡፡


## 2.2.1. ባለ ሁለት አውታረ መጠን ያላቸው ዝርግ ቅርጾችን መሳል እና ማቅለም

ተፈጥሮአዊ የሆኑ ባለ ሁለት አውታረ መጠን ቅርጾች (ዝርግ ቅርጾች) ስንል የቤትና የዱር እንስሳት ፣ ተራሮች ፣ ዛፎች(ደኖች) ፣ ወንዞችና ዳመና ፣ ክዋክብት ጸሐይና ጨረቃ በእየታዊ ጥበብ ሲገለጹ ያለምንም ብርሃንና ጥላ በነጠላ መስመር (በንድፍ) ብቻ ይሠራሉ፡፡




ምስል 2.10: ተፈጥሯዊ የሆኑ ባለ ሁለት አውታረመጠን ዝርግ ቅርጾች፡፡

ለሁለት አውታረ መጠን ዝርግ ቅርጽ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁስ



ምስል 2.11: ሰው ሠራሽ ባለሁለት አውታረመጠን ዝርግ ቅርጾች

ስዕል ባለሁለት አውታረ መጠን ዝርግ ቅርጽ የቤት አይነቶች



ምስል 2.12: ስዕል ባለሁለት አውታረ መጠን ዝርግ ቅርጽ

## 2.2.2. ባለሦስት አውታረ መጠን ቅርጾችን መሳል እና ማቅለም

ባለሦስት አውታረመጠን ቅርጽ ወይም ቁስ ማለት የሚዳሰስ ፣ የሚጨበጥ እንዲሁም ርዝመት ፣ ስፋት ፣ ጥልቀት ያለው አካል ማለት ነው፡፡ ባለሦስት አውታረመጠን ቅርጽ ብርሃን ባረፈበት ተቃራኒ አቅጣጫ ጥላ የሚፈጥር ነው፡፡


**ለምሳሌ:-** ተፈጥሮአዊ የሆኑ ባለሦስት አውታረመጠን ቅርጽ የዱር እንስሳት፣ ተራሮች ፣ ዛፎች (ደኖች) ፣ ወንዞችና ዳመና፣ ክዋክብት ፣ ጸሐይና ጨረቃ በእይታዊ ጥበብ ሲገለጹ ከነሙሉነታቸው ነው፡፡

**ለምሳሌ:-** ተፈጥሮአዊ የሆኑ ባለ ሦስት አውታረ መጠን ቅርጾች ስእላዊ መግለጫዎች፡፡



ምስል 2.13: ተፈጥሯዊ የሆኑ ባለ ሦስት አውታረ መጠን ቅርጾች ስእላዊ መግለጫዎቸ

እንደዚሁም ሰውሰራሽ የሆኑ ባለሦስት እውታረመጠን ቅርጾች ሙሉ ሲሆኑ ርዝመት ፣ ስፋትና ጥልቀት ያላቸው ናቸው፡፡ በላያቸው ላይ ብርሃን ባረፈበት ተቃራኒ አቅጣጫ ጥላ ሲወድቅ ሙሉ ቅርጽ ወይም በለሦስት አውታረ መጠን ቀርጽ ይባላሉ፡፡



ምስል 2.14: ሰው ሰራሽ ባለሦስት አውታረመጠን ቅርጾች



ምስል 2.15: የጋሞ አካበቢ ባህላዊ የቤት አሰራር ዓይነቶች

ተፈጥሮኣዊ ሰው ሠራሽ ባለ ሦስት አውታረ መጠን ቅረጾች



ምስል 2.16: ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ ባለ ሦስት አውታረ መጠን ቅርፆች

## መልመጃ 4

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ**

2. ባለሁለት አውታረ መጠን ስንል ምን ማለት ነው?
3. ባለሦስትና ባለሁለት አውታረ መጠን ቅርጾች አድነትና ልዩነት ግለጹ::
4. ባለሦስት አውታረመጠን ስእሎችን እቤታችሁ ስላችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ::

## 2.3. መሰረታዊ ቀለማትን መቀላቀል እና ቀጥታ ህትመት

### መግቢያ

በዚህ ንዑስ ክ/ትምህርት መሰረታዊ ቀለማትን በመቀላቀል ሌሎች ሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን እንዴት ማግኘት እንደምንችል እና ቀጥታ ህትመት ሲባል

ምን እንደሆነ ከእይታ ጥበባት ማለትም ከቀለምቅብ ፣ ከንድፍ (በእርሳስ የሚሳል ስእል) ቅርጻ ቅርጽ ከመሳሰሉት አንፃር ተማሪዎችምይህንን የጥበብ ዓይነት በቀላሉ በአካባቢያቸው ከሚገኙ ቁሶች መስራትና መተግበር መማር ያስችላቸዋል፡፡ በመሆኑም ይህንን በተግባር ለመከወን የሚስችላቸው አመቺ የመስሪያ ቦታና ቁሳቁሶች ያስፈልጋቸዋል፡፡

ተማሪዎች መስራች ቀለማትን እርስ በእርሳቸው ሲቀላቅሉ ሌላ ቀለም ማለትም ሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን ማግኘት ሲቻል እንደገና አንደኛ (መስራች) ቀለማት ከሁለተኛ ደረጃ ቀለማት ጋር ሲቀላቀሉ ሦስተኛ ደረጃ ቀለማትን እንደሚፈጥሩ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ቀለማትን በመቀላቀል የምናገኘው ውጤት ለምንስለው ስዕል ትክክለኛውን መልክ አስመስለን መቀባት እንድንችል ይረዳናል፡፡ ለዚህም ተግባር የሚረዱን ከአካባቢያችን በቀላሉ ከሚገኙ ቁሶች መቀቢያዎችን (ቡርሾችን) መስራት ከሚቻልባቸው መካከል ለምሳሌ ከዶሮ ላባ ፣ ከእንሳት ጸጉር(ጭራ) ፣ ከቃጫ ወዘተ... ከመሳሰሉት ቀጭን አንጨት ወይንም ጭራሮ ጫፍላይ በማሰር ለቀለም መቀቢያነት መጠቀም ይቻላል፡፡

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ የሚጠበቅባቸው፡-**

- መሰረታዊ ቀለማትን በመቀላቀል ሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን ይፈጥራሉ
- ህትመትን ከሌሎች የእይታ ጥበባት ማነጻጸር፡፡
- ለቀጥታ ህትመት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን መለየት፡፡
- ለቀጥታ ህትመት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት፡፡
- ከአካባቢ ከሚገኙ ቁሳቁሶች ቀጥታ ህትመትን ማተም፡፡

**የማንቂያ ጥያቄ ፡-**


1. ተማሪዎች ህትመት እና ቀጥታ ህትመት ልዩነታቸውን በቡድን ተወያይታችሁ በጽሁፍ አቅርቡ፡፡
2. ህትመት ከሌሎች የእይታ ጥበብ ዓይነቶች በምን እንደሚለይ ተወያዩ፡፡

## 2.3.1. መሰረታዊ ቀለማትን መቀላቀል

ተማሪዎች መስራች ቀለማትን እርስ በእርሳቸው ሲቀላቅሉ ሌላ ቀለም ማለትም ሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን ማግኘት ሲቻል እንደገና አንደኛ (መስራች)

ቀለማት ከሁለተኛ ደረጃ ቀለማት ጋር ሲቀላቀሉ ሦስተኛ ደረጃ ከለማትን እንደሚፈጥሩ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ቀለማትን በመቀላቀል የምናገኘው ውጤት ለምንስለው ስዕል ትክክለኛውን መልክ አስመስለን መቀባት እንድንችል ይረዳናል ለዚህም ተግባር የሚረዱን ከአካባቢያችን በቀላሉ ከሚገኙ ቁሶች መቀቢያዎችን (ብሩሾችን) መስራት ከሚቻልባቸው መካከል ለምሳሌ ከዶሮ ላባ ፣ ከእንስሳት ጸጉር(ጭራ) ፣ ከቃጫ ወዘተ... ከመሳሰሉት ቀጭን አንጨት ወይንም ጭራሮ ጫፍላይ በማሰር ለቀለም መቀቢያነት መጠቀም ይቻላል፡፡

መስራች ቀለማት እርስ በርሳቸው ወይንም አንዱ ከሌላው ጋር ሲቀላቀል ሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን ይመሰርታሉ፡፡




ብርቱካናማ

አረንጓዴ

ወይንጠጅ

ምስል 2.17: የመስራች ቀለማት ውጤት

## መልመጃ 4

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ**


1. ቀይ ቀለም + ቢጫ ቀለም = ----------------?
2. ቀጥታ ህትመት ማለት ምን ማለት ነው?
3. ሸካራነት ያላቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?

## 2.3.2. ቀጥታ ህትመት

ቀጥታ ህትመት ማለት አንድን ተፈጥሯዊ የሆነ ቁስ በአካሉ ላይ ለቀጥታ ህትመት አመቺ የሆነ ሸካራነትና ለስላሳነት እንዲሁም መስመሮች የሚገኙባቸው ተፈጥሮአዊ አሊያም ሰው ሰራሽ ነገሮችን ምንም ተጨማሪ ዲዛይን ሳይታከልበት በቀጥታ ቀለም በመቀባት በንጹህ ወረቀት ላይ ወይንም በንጹህ ጨርቅ ላይ ማተም ማለት ነው።

**ለምሳሌ፡-** ከተፈጥሮ ሸካራነት ያላቸውን የዛፍ ቅርፊቶች ፣ የተለያዩ የቅጠል ዓይነቶች ፣ የጣት አሻራ ወዘተ...

- ከሰው ሠራሽ የጫማ መርገጫ (የጫማ ሶል) ፣ የጠርሙስ ክዳኖች ፣ የጆኒያ ቁርጥራጭ ፣ ሸካራነት ያላቸው ጨርቃ ጨርቆች ይጠቀሳሉ።



ምስል 2.18: በአከባቢያችን ከሚገኙ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ቁሶች ቀጥታ ህትመትን የሚያሳይ ስዕል

## መልመጃ ሁለት

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ**

1. ለቀጥታ ህትመት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ግለጹ
2. ቀጥታ ህትመት ከሌሎች የዕይታ ጥበባት አይነቶች በምን ይለያል።
3. የህትመት ጠቀሜታን በዝርዝር ጻፉ።

## 2.4. በተውኔት፣ በተንቀሳቃሽ ምስሎችና ፎቶዎች መልዕክቶችን ማስተላለፍ

### መግቢያ

ተማሪዎች መልዕክት ማለት ምን ማለት ነው? መልእክት ስንል መናገር ፣ መስማት (ማዳመጥ) ፣ ማየት (መመልከት) ፣ መስጠት ፣ መቀበል የመሳሰሉት የሰውልጆች በየእለቱ ከሚያከናዉኗቸውና ኑሮዋቸውን ከሚመሩበት መንገድ አንዱ በመሆኑ ይገለገሉበታል፡፡ በመሆኑም በዕይታ ጥበብ ውጥም መልዕክቶች በተለያዩ መንገዶች ከአንዱ ወደሌላው በመተላለፍ ታሪክን ፣ ባህልን ፣ ትምህርትን ወዘተ... ከትውልድ ወደ ትውልድ በማስተላለፍ ለአንድ ሀገር እድገት ከፍተኛ ድርሻን ከመወጣት ባሻገር በዚህ ሙያ ለሚተዳደሩ ዜጎች የገቢ ምንጭ ከመሆኑም ባሻገር የእውቀት የሚሸጋገርበት መንገድ ነው፡፡

### ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ የሚጠበቅባቸው

- የመልዕከት ምንነትን መግለጽ፡፡
- መልዕክት የሚተላለፍባቸውን መንገዶች መዘርዘር፡፡
- ቀላል ፎቶ የማንሳት ዘዴን ይረዳሉ፡፡
- በፎቶ ውስጥ እንዴት መልክቶችን ማስተላለፍ እንዳለባቸው ይረዳሉ፡፡

### የማንቂያ ጥያቄ

1. ተማሪዎች በቡድን ሆናችሁ መልዕክቶች የሚተላለፉባቸውን መንገዶች በጋራ ተወያይታችሁ በቡድን አቅርቡ
2. በአካባቢያቹ የምታውቁትን መልዕክት ማስተላለፍያዎችን በስዕል ሠርታችሁ አቅርቡ፡፡

### 2.4.1. በፎቶ ያሉ መልዕክቶች

ከዕይታ ጥበባት አንዱ የተንቀሳቃሽ ምስሎችና ፎቶዎች ተግባርና ክንውኖች የህብረተሰቡና ማህበረሰቡን የአኗኗር ዘይቤና ማህበራዊ ግንኙነቶችና እንዲሁም ወግ ባህል ታሪክና ሁለንተናዊ ገጽታዎችን ከሌሎች በአገራችን ላሉ ማህበረሰቦች ይህን መልካም ባህልና ታሪክ እንዲሁም በሚመዘገቡና ተቀርጸው በሚቀመጡ መዛግብቶችና የምስል ማከማቻዎችና ማስቀመጫዎች

በእይታዊ ጥበብ አማካኝነት መልእክቶች በቀላሉ ከመተላለፋቸውም ባሻገር መረጃና ትምህርት ይሰጣሉ።

**ለምሳሌ፡-**

- ታሪካዊ ክንዋኔዎች
- ባህላዊ ክንዋኔዎች
- መንፈሳዊ ክንዋኔዎች

## ታሪካዊ ክንዋኔዎች

ኢትዮጵያዊያን ቅድመ አያቶቻችን የሀገራችን ዳር ድንበር ለማስክበር ከጠላት ጋር ያደረጉትን ተጋድሎ በተለያዩ የሥነ-ጠበብ መገለጫዎች አንዱ የዕይታ ጥበብ ሲሆን በዚህ ጥበብ የጀግኖችን ተጋድሎ ፣ ጊዜውን የሚያሳዩ የውጊያ መሳሪያዎች ጦር ፣ ጋሻ ፣ ጎራዴ እና የወቅቱ ዘመናዊ መሳሪዎች እንዲሁም የአገር ፍቅር የሚገለጽበት ነው። በአጠቃላይ የተጋድሎ ቦታና አካባቢ በሚያሳዩ የሥነ-ጥበብና የእይታ ጥበብ እንዲሁም በፎቶና በተንቀሳቃሽ ምስሎች መልዕክቶችን ማስተላለፍ ይችላሉ።




ምስል 2.19: የኢትዮጵያ ጀግኖች አገራቸውን ከጠላት ወረራ የታደጉበትን የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ

**ባህላዊ ክንዋኔዎች፡-** በአገራችንና በአካባቢያችን የሚገኙ ማህበረሰቦች ወቅታዊና ባህላዊ ክንዋኔዎችን ይተገበራሉ።

**ለምሳሌ፡-**

- ሠርግ
- ዘመን መለወጫ (እንቁጣጣሽ )
- ሀዘን (ለቅሶ)
- ልደት
- ምረቃ (ምርቃት) የትምህርት ፤ የቤት እና በማህበረሰቡ የተሠሩ የተለያዩ የልማት ሥራዎችን በሚያሳዩ የሥነ-ጥበብና የእይታ ጥበብ እንዲሁም በፎቶና በተንቀሳቃሽ መስሎች መልዕክቶች መተላለፍ ይችላሉ፡፡



ምስል 2.20: እና ምስል 2.21 ባህላዊና ዘመናዊ የሠርግ ስነስርአት የሚያሳይ ምስል፡፡



ምስል 2.21: አገር በቀል ክንዋኔዎች ከሆኑት አንዱ ቡሄበሉ (ሆያሆየ) የሚገልጽ ስዕል፡፡



ምስል 2.22: የዘመን መለወጫ የአዲስ አመት መቀበያ (አበባ አየሽ ወይ) በህጻናት ሲዘመር

### ✯ ሐይማኖታዊ ( መንፈሳዊ ) ክንዋኔዎች

በአገራችንና በአካባቢያችን በሚገኙ ማህበረሰቦች የተለያዩ ሐይማኖታዊና መንፈሳዊ ክንውኖች ይተገበራሉ:: በመሆኑም ማህበረሰቡ እንደ የአይነቱ የራሱን ሐይማኖታዊ እሴቱን በመጠበቅ ሐይማኖታዊ በዓላትን ያከብራል፡

**ለምሳሌ፡-**

- ✯ በክርስትና፡- የልደት፤ የጥምቀት፤ የስቅለት፤ የትንሳኤ (ፋሲካ) እና ወዘተ...
- ✯ በሙስሊሞች፡- የመውሊድ፤ አረፋ፤ ኢድአልፈጥር፤ ኢድ አልድሃ እና ወዘተ...

እነዚህ አገራዊና ማህበረሰባዊ እንዲሁም አካባቢያዊ የሆኑ ሐይማኖታዊና መንፈሳዊ ትውፊቶችን በሚያሳዩ የሥነ-ጥበብና በፎቶና በተንቀሳቃሽ መስሎች መልዕክቶች መተላለፍ ይችላሉ::



ምስል 2.23: ሐይማኖታዊ የጋብቻ ስነ-ስርዓት



ምስል 2.24: ከሐይማኖታዊ ክንዋኔዎች አንዱ ከሆነው የጥምቀት በዓልን የሚገልጽ ስዕል

## መልመጃ 6

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ**

1. የፎቶዎችን ጥቅም ጥቀሱ
2. የተለያዩ ባህላዊ ክንውኖችን ዘርዝሩ

## 2.4.2. በተውኔት ውስጥ ያሉ መልዕክቶች

በዚህ ንዑስ ክ/ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች ተውኔትን በመጠቀም እንዴት መልዕክቶችን ማስተላለፍ እንደሚቻል የሚያወቁበት ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በምዕራፍ አንድ ስር የተማሩትን የትራጀዲ እና ኮሜዲ ደራማዎች ፅንሰ ሐሳብ መነሻ በማድረግ በአካባቢያቸው እና በቤተሰቦቻቸው ዙሪያ የሚመለከቱትን ወደ ድራማ በመቀየር እና ገፀ-ባህርያትን በመላበስ እየተወኑ ለክፍል ጓደኞቻቸው እና ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ያቀርባሉ፡፡

### ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች�:-

- በተውኔት /ድራማን/ ተጠቅመው መልዕክትን በድራማ ያስተላልፋሉ፡፡
- በትውን ጥበባት እንዴት መልክት ማስተላለፍ እንደሚቻል ይረዳሉ፡፡

### የማነቃቂያ ጥያቄ

- ተውኔት ምንድነው?

⚡ እንዴት በተውኔት መልዕክት ማስተላለፍ ይቻላል?

ተውኔት የምንለው ቃል በምዕራፍ አንድ እንደተመለከትነው ድራማ የሚለውን ቃል ይወክላል። ድራማ ከመባሉ በፊት ጨዋታ እንደሚባል ሁሉ ተውኔትም ድራማን በመወከል ያገለግላል።

ድራማ ወይም ተውኔት በመድረክ ላይ ተመልካቶችን በቀጥታ በማግኘት የሚከውን የትውናና ዕይታ ጥበብ ዘርፍ ውስጥ የሚገኝ ነው።

በተውኔት መልዕክቶችን ማስተላለፍ ሲባል ተውኔት የገሃዱን አለም ነፀብራቅ ለመድረክ በሚመጥን መልኩ የዕለት ከዕለት ኑሮን መጥኖ ወደ መድረክ ማቅረብ ሲለሆነ በተውኔት በርካታ ነጥቦችን መልዕክቶችን ማስተላለፍ ይቻላል።

የተለያዩ ትምህርቶችን መልዕክቶችን ቀጥታ ከማስተላለፍ ይልቅ በድራማ (በተውኔት) እየተዝናኑ መልዕክቶችን እንዲያዳምጡ ማድረግ የተሻለ ነው።

### 2.4.3. በተውኔት እንዴት መልዕክት ማስተላለፍ ይቻላል

በምዕራፍ አንድ እንደተመለከትነው ድራማ ወይም ተውኔት በሁለት ይከፈላ አዝናኝ (አስቂኝ) እና አሳዛኝ ተብለው። በእነዚህ ሁለቱ ክፍሎች ውስጥ የድራማ ታሪክ ወይም ድርሰት ይዘጋጃል። በተዘጋጀው ታሪክ ወይም ድርሰት ድንገት ፈጥረን ወይም ምጥን ተውኔትን ባለ አንድ ገቢር አልያ የሙሉ ጊዜ ተውኔት ይዘጋጃል። በተዘጋጀው ጽሑፍ መሠረት ገፀ-ባህሪ በመከፋፈል አዘጋጅ ወይም ቡድኑን የሚመራ ሰው በመምረጥ የልምምድ ጊዜ በማውጣት መለማመድ ቃለ ተውኔቱን ማጥናት ስሜት ሰጥተው ድርጊቶች ጋር መተወን ያስፈልጋል። ደጋግሞ መለማመድ በደንብ ስሜቶች ድርጊቶችን ያለ እንከን ለመተወን አስፈላጊ አልባሳት የገፀ-ቅብ (ሜካፕ) ፣ ቁሳቁስ ፣ የድምጽ ግብዓት ፣ መብራት በመጠቀም አላስፈላጊ የሆኑትን በመተው በአዳራሽ ወይም ተመልካች በተሰበሰበበት መድረክ ማቅረብ ይቻላል።

## መልመጃ 7

1. ተማሪዎች በቡድን በመሆን አስቂኝ ምጥን ተውኔት መርጣችሁ አዘጋጅታችሁ አቅርቡ

2. በቡድን በመሆን አሳዛኝ ምጥን ተውኔት አዘጋጅታችሁ አቅርቡ

**የተውኔት ዓይነቶች**

ተውኔቶች በጊዜ ይከፋፈላሉ፡፡ ዓይነቶችም በዛው ልክ ይለያሉ ማለትም ባለሙሉ ጊዜ ተውኔት እና መካለኛ ናቸው፡፡ ረጅም ጊዜና ሁለት እና ከዚያ በላይ ገቢር ያሉበት ባለአንድ ገቢር የምንለው ዳግም በአንድ ገቢር የታጠረ መካከለኛ የጊዜ ቆይታ ያለው ነው፡፡

**ድንገቴ ፈጠራ**

ድንገት ፈጠራ የተፃፈ ተውኔት ሳይኖር መጀመርያ፣መሀልና መጨረሻ ኖሮት ማለትም ታሪክ ብቻ እና ገፀ-ባህርያት ተከፋፍለው የተወሰኑ ድርጊቶችን ተነጋግረው ያለ ቃለ ተውኔት በርዕስ ጉዳዩ ላይ ተዋንያኖች ከራሳቸው እየፈጠሩ ድርጊቶችን ጨምረው የሚተውኑት የተውኔት ዓይነት ነው፡፡

**ሙከራ**

ተማሪዎች የሚከተለውን ታሪክ መሰረት አድርጋችሁ ቃላትን ከራሳችሁ ፈጥራችሁ በታሪኩ ቅደም ተከተል በድንገቴ ፈጠራ ተውኑ፡፡

**ታሪክ**

አባት እናት ሁለት ወንድ እና ሴት ልጆች አንድ ላይ ይኖራሉ፡፡ ጥዋት ሲነሱ እናት ቁርስ ስታቀራርብ ልጆችን እናት አባታቸውን እንዲያስታጥቡ ስታዛቸው፡፡ አንች አስታጥቢ አንተ አስታጥብ እየተባባሉ ይጨቃጨቃሉ፡፡ እናት ከጓዳ ወታ ለምን እንደሚጣሉ ስትጠይቅ አንተ አንች አሳታጥቢ ተባብለው እንደሆነ ሲነግሯት እናት በጣም አዝና ሁለቱም ያደረጉት ትክል እንዳልሆነ ነግራቸው፡፡ ልጆች ሲታዘዙ እንደሚያድጉ ወደ ፊትም መልካም ነገር እንደሚገጥማቸው መሆን የሚፈልጉትን ታዘው ካደጉ መሆን እንደሚችሉ ስትነግራቸው እናታቸው ይቅርታ ጠየቁ፡፡ ተሽቀዳድመው እሷ በጆግ ውሃ እሱ ማስታጠቢያ ሳህኑን ይዞላት አባታቸውን ያስታጥባሉ አባታቸው ግንባራቸውን ስሞ ይመርቃቸዋል እደጉ ተመንደጉ ያሰባችሁት ሁሉ ይሙላላችሁ ለሀገራችሁ ኢትዮጵያ ዘብ የምትቆሙ እድገቷን የምታፋጥኑ ከጥላቶቿ የምትጠብቁ ሆናችሁ እደጉ፡፡ ወንዱ ልጅ አባዬ ኢትዮጵያ ሀገራችን ጠላቶቿ እነማን ናቸው? እናት ልጆቼ ከውጭ ሆነው ስለሀገራችን መጥፎ

የሚናገሩ የሚያደርጉ ፈረንጆች አሉ ነገር ግን ፈረንጆች ሁሉም ጠላት አይደሉም ለኢትዮጵያ ሀገራችን መልካም የሚያደርጉ ፈረንጆችም አሉ:: ሴት ልጅ አድጋ የሀገራችንን ጠላቶች ማጥፋት ነው ምፈልገው:: አባት ልጆች የሀገራችን ጠላቶች ማጥፋት የምንችለው ባለንበት በርትተን ጠንክረን ጎብዘን ከሰራን ድህነታችንን ካጠፋን ከጎበዝን ጠላቶቿ ሁሉ በራሳቸው ጊዜ ይጠፋሉ:: እናት ጠንክራችሁ ጎብዛችሁ እየተማራችሁ እየሰራችሁ እርስ በእርሳችሁ ከተዋደዳችሁ ጠላት አይደፍረንም ይሏቸዋል:: አባት በሉ እኔ ስራ ልግባ እናንተን ት/ቤት ልሸኛችሁና አንችም ተነሽ እንሂድ (ተነስተው ደብተራቸውን ይዘው አብረው ይወጣሉ)::

## የትምህርቱ ማጠቃለያ

ድምፆች ባላቸው ባህሪያት መደበኛ (ሙዚቃዊ) እና መደበኛ ያልሆኑ (ኢ-ሙዚቃዊ) ብለን በሁለት እንከፍላቸዋለን::

መደበኛ (ሙዚቃዊ) ድምፆች የምንላቸው ውስን በሆነ የድምፅ እርግብግብታ የሚፈጠሩ እና ለጆሮ የማይረብሹ ወይም የሚመቹ ሙዚቃዊ ድምፆች ሲሆኑ እነዚህንም ድምፆች በአካባቢያችንም ሆነ በአለማችን ለሙዚቃ ስራ ምንጠቀምባቸው ናቸው::

መስራች ቀለማት እርስበራሳቸው ወይም አንዱ ከሌላውጋር ሲቀላቀል ሁለተኛደረጃ ቀለማትን ይመሰርታሉ:: ቀጥታ ህትመት ማለት አንድ ተፈጠሮአዊ የሆነ ቁስ በአካሉ ላይ ለቀጥታ ህትመት አመቺ የሆነ የሸካራነትና ልስላሴነት እንዲሁም መስመሮች የሚገኙባቸው ተፈጥሯዊ ወይም ሰውሰራሽ ነገሮችን ምንም ተጨማሪ ዲዛይን ሳይታከልበት ቀለም በመቀባት በቀጥታ በወረቀት ወይም በጨርቅላይ ማተም ነው::

ለምሳሌ ያህል በገበያ አካባቢ የምንሰማቸው ሁካታዎች ፣ ከመጠን በላይ ጮክ ብሎ የሚሰማ ሙዚቃ ፣ የትራፊክ መጨናነቅ በሚበዛበት አካባቢ የሚሰሙ የመኪና ጥሩንባወች ወ.ዘ.ተ. ሲሆኑ እነዚህ አይነት ድምፆች አዕምሮን የሚረብሹ እና ጤናንም የሚጎዱ ድምፆች ናቸው::

በአለማችን ውስጥ በርካታ ማህበረሰቦች ይገኛሉ:: እነዚህ ማህበረሰቦችም


የራሳቸው የሆነ ወግ ፣ ባህላዊ ውዝዋዜ/ዳንስ/ ፣ ሙዚቃ ወ.ዘ.ተ አሏቸው፡፡ በዚህም አስተሳሰባቸውን ፣ ፍላጎታቸውን ፣ አኗኗራቸውን ፣ ሀዘናቸውን ፣ ደስታቸውን ወ.ዘ.ተ. ለመግለፅ ከሚጠቀሙባቸው የጥበብ መንገዶች ውስጥ አንደኛው የጥበብ መንገድ ሙዚቃ ነው፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**ትዕዛዝ 1፡ ከዚህ በታች ለተዘረዘሩ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ስጡ**

1. ድምፅ እንዴት ይፈጠራል?
2. ስንት አይነት ድምፆች አሉ?
3. ሙዚቃዊ/መደበኛ/ ድምጽ የምንላቸው ምን አይነት ድምፆችን ነው?
4. ኢ-ሙዚቃዊ/ኢ-መደበኛ/ ድምጽ የምንላቸው ምን አይነት ድምፆችን ነው?
5. ድምፅ ማለት ምን ማለት ነው?
6. ሃለካ የምንለው የሙዚቃ መሳሪያ ከምን ይሰራል?
7. በቀድሞ ጊዜ ነገስታት አዋጅ ለማወጅ እና በጦርነት ወቅት መልዕክት ለማስተላለፍ ይጠቀሙበት የነበር የምት የሙዚቃ መሳሪያ ምን ይባላል?
8. ከከበሮ ጋር ተመሳሳይነት ያለው የምት የሙዚቃ መሳሪያ ማን ይባላል?

**ትዕዛዝ 2፡-ከዚህ በታች የተቀመጡትን የኖታ እና የእረፍት ምልክቶች በጭብጨባ እና በእረፍት ለማንበብ ሞክሩ**



9. በድንገቴ ፈጠራ የምንሰራው ተውኔት ምንን መሰረት በማድረግ ነው?

**ትዕዛዝ 3፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ**

1. ቀላል የሆኑ ባለሁለት አውታረመጠን ዝርግ ቅርጾች ማለት እይታዊ ጥበብ ውስጥ የሚገለጹት በውጫዊ መስመር ነው፡፡
2. ባለሁለት አውታረመጠን ዝርግ ቅርጾች በተፈጥሯዊ እና በሰው ሠራሽ ቁሶች በነጠላ መስመር በመንደፍ የሚገለጽበት መንገድ ነው፡፡
3. ባለ ሦስት አውታረመጠን ቅርጽ ወይም ቁስ ማለት የሚዳሰስ፤የሚጨበጥ፤ እንዲሁም ርዝመት፤ ቁመት፤ጥልቀት ያለው አካል ማለት ነው፡፡
4. መስራች ቀለማት እርስበራሳቸው ወይም አንዱ ከሌላው ጋር ሲቀለቀል ሦስተኛ ደረጃ ቀለማትን ይመሰርታሉ፡፡
5. ሰማያዊ ቀለም ከቢጫቀለም ጋር ሲቀላቀል የሚገኘው ውጤት ብርቱካናማ ቀለም ይሆናል፡፡
6. ድንገቴ ፈጠራ ቃለ-ተውኔት ሳይኖር በታሪክ ብቻ የሚተወን ነው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. ባህላዊ አውድ

### መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ በቀደሙት የጥበብ አባቶቻችን የተሰሩ የእይታና ትውን ጥበባትን የምንቃኝበት ነው፡፡ የሰው ልጅ ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ በኑሮው ውስጥ የሚገጥሙትን የተለያዩ የደስታ ፣ የሐዘን ፣ የፍቅር ወ.ዘ.ተ. አጠቃላይ የኑሮ ውጣ ውረዶችን በተለያዩ የእይታ እና የትውን ጥበባት በመግለፅ አኗኗራቸውን ሲያንፀባርቅ ይታያል፡፡

የሰው ልጆች እንደየ አካባቢያቸው የአየር ንብረት ሁኔታ እና አኗኗር የተለያየ አይነት አለባበስ ፣ የቤት አሰራር ፣ ባህል ፣ ውዝዋዜ ፣ ሙዚቃ ወ.ዘ.ተ. አሏቸው፡፡ ይህም ሲባል ሰዎች ስሜታቸውን በሙዚቃ እና መሰል የጥበብ ስራዎች ከመግለፅ ባለፈ በአለባበሳቸውም ስሜታቸውን ማንፀባረቅ ይችላሉ፡፡

በዚህ ምዕራፍም ቀደምት አባቶቻችን የትውን እና እይታ ጥበባትን ተጠቅመው የሰሯቸውን ስራዎች ከማየት ባለፈ የአለባበስ እና የቤት አሰራራቸውን ለመቃኘት እንሞክራለን፡፡

**ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች**

- በማህበረሰባቸው አካባቢ የሚዜሙ ቀደምት የባህል ሙዚቃዎችን ምን ይመስሉ እንደነበር ይቃኛሉ ይጫወታሉ፡፡
- በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ውስጥ የሚታዩትን የባህል አለባበስ ይቃኛሉ፡፡
- በቀደምት የጥበብ አባቶች የተሰሩ የትውን እና እይታ ጥበባት ስራዎችን ከአሁኑ ዘመን ጋር ያወዳድራሉ፡፡
- በአካባቢያቸው የሚታዎቁ ባህላዊ ዜማዎችን ፣ ዘፋኞችን እና ስራዎቻቸውን ይቃኛሉ
- በአካባቢያቸው የሚታዎቁ ባህላዊ ውዝዋዜዎችን እና ሙዚቃዎችን የቀደሙትን ከአሁኑ ዘመን ጋራ በማወዳደር ይለያሉ፡፡
- የተለያዩ ተፈጥሮ መስህቦችን እና ባህላዊ ቦታዎችን በመጎብኘት የፅሑፍ ዘገባ ያቀርባሉ፡፡

## 3.1. ባህላዊ ብዝሀነት ባለፈው እና በአሁኑ ጊዜ በእይታና የትውን ጥበባት ሲቃኝ

### መግቢያ

ባህል ማለት በአገራችን አካባቢችን በሚገኙ ማህበረሰቦችና ህዝቦች የሚተገበርና በየጊዜው የሚከወን ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም በማህበረሰቡ ውስጥ እንደ የማህበረሰቡ አኗኗርና ማህበረሰቡን የሚገልጹ የሀዘን ፣ የሠርግ እና የተለያዩ ባህላዊና ሐይማኖታዊ እንቅስቃሴዎችን በአካባቢያችንና በአገራችን እንዲሁም በመላው ኢትዮጵያ ባህላዊ ብዝሀነትን ጠብቆ በማህበረሰቡ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ ባህላዊ ብዙሀነት ባለፈውና በአሁኑ ጊዜ በእይታ ጥበብ ሲቃኝ ማህበረሰቡ በዘመኑና ጊዜው ከተማረና ከሰለጠነ አኗኗሩ ስለሚቀየር ባህሉም ከባለፈው የአሁኑ ጊዜ ዘመናዊነትን የተላበሰ በመሆኑ ባለፈው ጊዜ ይተገበር የነበረው የቤት አሠራር ፣ አለባበስ ፣ አመጋገብ ፣ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች በጠቃላይ ከዘመኑ ስልጣኔ አኳያ ስለሚቀየር በእይታ ጥበብ አኳያ ሲቃኝ የባለፈውና የአሁኑ ልዩነት ይታይባቸዋል፡፡ በመሆኑም ልዩነቶችም በተለያዩ

የስነ-ጥበብና የእይታ ጥበብ አማካኝነት ተቀርጸው በመቀመጥ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸገሩ መደረግ አለባቸው፡፡

**ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ የሚጠቁ ውጤቶች**

- የባህላዊ ገለጻ ምንነትን መናግር
- ባህላዊ ገለጻና የእይታ ጥበብን ማነጻጸር
- ባህላዊ ገለጻዎች ከታሪክ ዐውድ ጋር ያላቸውን ግንኙነት መረዳት
- ባህላዊና ታሪካዊ የእይታ ጥበቦችን መጠበቅና መንከባከብ

## ማንቂያ (መሪ ተግባራት)

1. ባህላዊ ገለጻ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ተማሪዎች ባህል ስንል  ምን ማለት ይመስላችኋል?

ታሪክና ባህል በእይታ ጥበብ እንዴት ይገለጻሉ የሚሉትን ጥያቄዎች ለተማሪዎች በቡድን ተወያይተው በቡድናቸው አለቃ አማካይንት እንዲያቀርቡ ማድርግ፡፡

ባህል ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱ የሆነው የእይታ ጥበብ ነው፡፡ በዚህ የእይታ ጥበብ በሀገራችን የሚገኙ ጠቃሚ የሆኑ ባህላዊ እሴቶችን መዝግቦና ቀርጾ ያስቀራል፡፡ ካለፈው ትውልድ የተላለፉትን የእይታ ጥበባትና የተለያዩ የኪነ-ጥበብና የሥነ-ጥበብ ውጤቶች ከአሁኑ እና ዘመኑ ከደረሰበት ስልጣኔ ደረጃ አንጻር ጎን ለጎን በማስኬድና በማስቀመጥ የማህበረሰቡን የአኗኗር ፣ የአለባበስ ፣ ሀዘንና ደስታ እንዲሁም የቤት አሰራራቸውን ጨምሮ በተለያዩ የእይታ ጥበባትና የኪነ-ጥበብና የሥነ-ጥበብ አመዘጋገብ ስልቶች ቀርጾ በማስቀመጥ እንደ ቅርስና እንደ ታሪክ ዐውድ ከዘመን ዘመን ይሻገራል፡፡ ተማሪዎችም ባህላዊ እሴትንና ታርክን መንከባከብና መጠበቅ እንዲችሉ መማርና ማወቅ አለባቸው፡፡

## የተግባር መልመጃ 1

3. ተማሪዎች አራት ቡድን በመመስረት እና የባህል አልባሳትን በመልበስ ቀደም ያሉ አባቶች በተለያዩ ክብረ በዓላት ላይ ይጫወቷቸው የነበሩ የተለያዩ ባህላዊ ዜማዎችን ለክፍል ጉደኞቻችሁ አቅርቡላቸው፡፡



ምስል 3.1: ባህላዊ ገለጻዎችን የሚያሳዩ ስዕሎች



ምስል 3.2: ባህላዊ ገለጻዎችን የሚያሳዩ ስዕሎች

## 3.1.1. ባህል ቅርስ እና የተፈጥሮ መስህቦች

ኢትዮጵያ የበርካታ ባህል እና የተፈጥሮ መስህቦች ያሉባት ሀገር ናት፡፡ እነዚህንም የባህል እና የተፈጥሮ መስህቦች በተለያዩ የሃገራችን ቦታዎች እናገኛቸዋለን፡፡


ኢትዮጵያ በዓለማችን እጅግ ጥንታዊ የስልጣኔ ታሪክ ያላት ክርስትናን እና እስልምናን ፣ የዋቄፈና እምነትን ጨምሮ የበርካታ ሀይማኖት ተከታዮች በፍቅር እና በአንድነት የሚኖሩባት ድንቅ አገር ናት፡፡ በቅድመ ሰው ዘር ጥናትም የመጀመሪያ የሰው ዘር መኖሪያ /መገኛ/ ፣ ቡናን ለዓለም ያስተዋወቀች የበርካታ ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሯዊ ቅርሶች ባለቤት የሆነች አገር ናት፡፡ አገራችን በተለየ ሁኔታ የቋንቋ እና የባህል ብዝሃነት የሚታይባት ባህላዊ እና ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤዎች በኪነ-ጥበብ ፣ በስነ-ጥበብ እና በእደ-ጥበብ አዋዝታ ማራኪ ዕይታዎችን የፈጠረች አስደናቂ እና አስደማሚ አገር ናት፡፡ ለዚህም የሥልጣኔ ፣ የባህል እና የታሪክ ባለቤት ለመሆኗም ከአስራ ሁለት በላይ የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ቅርሶች በዓለም አቀፍ መድረክ በዮኔስኮ በማስመዝገብ ታላቅነቱን ያስመሰከረች ሃገር ናት፡፡ ይህም የሰው ልጆች ሁሉ ቅርስ የሆኑ ሃብቶችን ያቀፈች የዓለማችን ድንቅ አገር ያደርጋታል፡፡

ኢትዮጵያ ካሏት እጅግ ብዙ የባህል ሀብቶቿ ውስጥ በማይዳሰሱ ቅርሶች ዘርፍ ሙዚቃው እና ውዝዋዜውን እናገኛለን፡፡ ሙዚቃ እና ውዝዋዜ እረገድ

ሀገራችን ያላት አቅም ከፍተኛ እና ቀደምት ከሚባሉት የሚመደብ ነው፡፡ የምዕራቡ አለም ዘመን የማይሽራቸው /ክላሲካል/ ብሎ የሚመፃደቅባቸውን የእነ ሞዛርት እና ቤትሆቨን ስራዎች በ14ኛው ክ/ዘመን ከመውጣታቸው በፊት ኢተዮጵያዊው የሙዚቃ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ጥልቅ እና መንፈስን የሚያድሱ እስከዛሬ ድረስ ዘመናትን የተሻገሩ ማህሌታዊ ዜማዎችን የደረሰው በ6ኛው መቶ ክ/ዘመን ነበር፡፡ አለም የሙዚቃ ድምፆችን በምልክቶች እየወከለ ዶ ፣ሬ ሚ…. እያለ እና የኖታ እና የእረፍት ምልክቶችን ቀርፆ ከመፃፉ ከብዙ መቶ አመታት በፊት ሊቁ ቅዱስ ያሬድ ጭረት፣ ድፋት ርክርክ፣ ውርድ፣ ይዘት፣ ድፋት፣ቅናት ወ.ዘ.ተ ብሎ የዜማ ምልክቶችን በመስራት /በመቅረፅ/ በመቋሚያ ዜማን መርቷል፡፡ ለዚህም ነው አገራችን የቀደምት ስልጣኔ ፈር ቀዳጅ የባህል እና የታሪክ ባለቤት የቋንቋ እና የባህል ብዝሃነት የሚታይባት ባህላዊ እና ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤዎች በኪነ-ጥበብ፣ በስነ-ጥበብ እና በእደ-ጥበብ አዋዝታ በማቅረብ ማራኪ ዕይታዎችን የፈጠረች አስደናቂ እና ውብ ሀገር ናት፡፡ ስለ ሃገራችን ኢትዮጵያ ይህንን ያህል ካልን በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን /በአካባቢያችን/ ያሉ ባህላዊ የውዝዋዜ እና የሙዚቃ ስራዎችን እንመልከት፡፡



ምስል 3.3: ሊቁ ቅዱስ ያሬድ ለንጉስ ገ/መስቀል በቤተ-መንግስታቸው ዜማ ሲጫዎትላቸው የሚያሳይ ምስል




ምስል 3.4: የቅዱስ ያሬድ የኖታ ምልክቶች

## የተግባር መልመጃ 1

1. ተማሪዎችን በአራት ቡድን በመክፈል እና የባህል አልባሳትን እንዲለበሱ በማድረግ ቀደም ያሉ አባቶች በተለያዩ ክብረ በዓላት ላይ ይጫወቷቸው የነበሩ የተለያዩ ባህላዊ ዜማዎችን ለክፍል ጉደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

## 3.1.2. ታሪካዊ ቦታዎች እና የተፈጥሮ መስህቦች

ታሪካዊ ቦታዎች የምንላቸው በቀድሞ ዘመን ይኖሩ የነበሩ ጥንት አባቶቻችን የሰሯቸው ስራዎች ሲሆኑ እነዚህ ጥንታዊ እና ታሪካዊ ቦታዎችን መጎብኘት የቀድሞውን ዘመን የሰዎችን አኗኗር እንድናውቅ እና እንድንረዳ ከማደረጉም በላይ የዛሬ ማንነታችንን እንድንረዳ ያደረጉናል፡፡ በሌላ በኩል የተፈጥሮ መስህቦች የምንላቸውም አምላክ /ፈጣሪ/ በኪነ ጥበቡ አስውቦ እና አሳምሮ የሰራቸው እና ያስቀመጣቸው ለመንፈስ እርካታ ለአዕምሮ ደስታን የሚያጎናፅፉ ውብ የተፈጥሮ መስህቦች ናቸው፡፡ በመሆኑም ማንኛውም የሰው ልጅ እነዚህን ታሪካዊ ቦታዎች እና የተፈጥሮ መስህቦች ከመጎብኘት እና ከማወቅ ባለፈ ሊጠብቃቸው እና ተንከባክቦ ለመጭው ትውልድ ሊያስረክባቸው ይገባል፡፡

**ከዚህ ክ/ትምህርት በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

- በሚኖሩበት አካባቢ ያሉ የተፈጥሮ መስህቦችን እና ታሪካዊ ቦታዎችን ይጎበኛሉ ይተዋወቃሉ፡፡
- በሚኖሩበት አካባቢ ያሉ የተፈጥሮ መስህቦችን እና ታሪካዊ ቦታዎችን እንዴት መጠበቅ እና መንከባከብ እንዳለባቸው ግንዛቤ ይይዛሉ፡፡
- የተፈጥሮ መስህቦችን እና ታሪካዊ ቦታዎችን በእይታና ትውን ጥበባት እንዴት ለሌሎች ማስተዋወቅ እንዳለባቸው መጠነኛ ግንዛቤ ይጨብጣሉ፡፡

## ሀ. ታሪካዊ ቦታዎች

### የማንቂያ ጥያቄ፡-

1. ከአሁን በፊት ተማሪዎች የጎበኟቸውን ታሪካዊ ቦታዎች መጠየቅ፡፡ የጎበኟቸው ቦታዎች የት እና መቼ እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ፡፡ ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡
2. በመኖሪያ አካባቢያቸው ምን አይነት ታሪካዊ ቦታዎች አሉ?
3. በምትኖሩበት አካባቢ ለሚገኙ ታሪካዊ ቦታዎች ምን አይነት እንክብካቤ ታደርጋላችሁ? ከሆነ እንዴት? እና በምን መንገድ?

ኢትዮጵያ የበርካታ ታሪኮች ባለቤት ናት፡፡ ቀደምት አባቶቻችን ከሰሯቸው ስራዎች መካከል የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ፤ የአክሱም ሃውልቶች የሐረር ግንብ ፤ የነጃሽ መስኪድ ፤ የሶፍ ዑመር ዋሻ ወ.ዘ.ተ. ከብዙ ጥቂቶቹ ሲሆኑ የአድዋ ድል የሚገኝበት የአድዋ ተራሮችም ከታሪካዊ ቦታዎች ውስጥ በዋነኝነት የሚጠቀስ ነው፡፡

ቀደም ባለው ጊዜ በዲራይታ “ሆርማ ቃሎ” ተብሎ ይጠራ የነበረው እና ሞስየ፣ ማሾሌ ፤ ኩስሜ ፤ ደራሼ የተባሉ ጎሳዎች የሚገኙበት በቀድሞው የጋሞ ጎፋ ዞን ውስጥ የሚገኘው የጋረዱላ ተራራ ደግሞ በደቡብ ኢትዮጵያ ውስጥ ከምናገኛቸው ቀደምት እና ታሪክ ጠገብ ቦታዎች አንዱ ነው ፡፡

ጋርዱላዎች እንደ ቀደምቶቹ የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ማዕከላዊ መንግስት ወደ አካባቢው ከመዝለቁ በፊት በራሳቸው የስልጣኔ ጎዳና ሐይማኖት ፤ ባህል ወግ እና የኢኮኖሚ ስርአት መስርተው ይኖሩ እንደነበር ታሪክ ይናገራል፡፡

በ1883 ዓ.ም ከአፄ ምኒሊክ የጦር አዝማቾች መካከል በራስ ሉዑል ሰገድ ይመራ የነበረው ጦር ሲዳሞን ካስገበረ በኋላ በደጃች ገነሜ አዝማችነት ወደ ጋርዱላ በመምጣት አካባቢውን የኢተዮጵያ ንጉሳዊ መንግስት አካል እንዳደረጉት ታሪክ ይናገራል፡፡ ራስ ልዑል ሰገድ አካባቢውን ከኢትዮጵያ ጋር ከቀላቀሉት በኋላ በቀጣይ ለሚያደርጉት መስፋፋት እንደ ዘመቻ መምሪያ / የዕዝ ማዕከል/ አድርገው የተጠቀሙት ታሪካዊውን የጋረዱላ ተራራ ነበር:: ዛሬ ጋረዱላ የሚለውን መጠሪያም የተገኘው ደራሼዎች "ሆርማ ቃሎ" የሚሉትን የሸዋ ኦሮሞ ዘማች ወታደሮች በኦሮምኛ "ካራ ዱላ" ወይም የዘመቻ መንገድ እያሉ በመጥራታቸው ነው፡፡

## መልመጃ 1

### ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ

1. ታሪካዊ ቦታዎች የምንላቸው ምን አይነት ቦታዎችን ነው?
2. የጋረዱላ ተራራ በየትኛው የኢትዮጵያ ክፍል እናገኘዋለን?
3. ታሪካዊ ቦታዎችን መጎብኘት ምን ጥቅም አለው?
4. ታሪካዊ ቦታዎችን መጠበቅ እና መንከባከብ ምን ጥቅም አለው ትላላችሁ? አስረዱ፡፡

## ለ. ተፈጥሯዊ መስህቦች

ተፈጥሯዊ መስህቦች የምንላቸው አምላክ /ፈጣሪ/ በኪነ-ጥበቡ አስውቦ እና አሳምሮ የሰራቸው እና ያስቀመጣቸው ለመንፈስ እርካታ ለአዕምሮ ደስታን የሚያጎናፅፉ ውብ የተፈጥሮ መስህቦች ናቸው፡፡ በመሆኑም ማንኛውም የሰው ልጅ እነዚህን ታሪካዊ ቦታዎች እና የተፈጥሮ መስህቦች ከመጎብኘት እና ከማወቅ ባለፈ ሊጠብቃቸው እና ተንከባክቦ ለመጭው ትውልድ ሊያስረክባቸው ይገባል፡፡ የተፈጥሮ መስህብ ያላቸውን ቦታዎች መጠበቅ እና መንከባከብ በተፈጥሮ መስህቦች ልናገኘው ከምንችለው የመንፈስ እርካታ እና የአዕምሮ ደስታ ባለፈ ንፁህ ፅዱ እና የተዋበ የመኖሪያ አካባቢ እንዲኖረን እና ከተለያዩ የተፈጥሮ አደጋዎች ፣ ከፍተኛ ሙቀት ጎርፍ የመሬት መሸርሸር ወ.ዘ.ተ ለመጠበቅ ያስችለናል፡፡

ከመምህራችሁ ጋር በመነጋገር በበጋ የእረፍት ጊዜያችሁ ሔዳችሁ ለመጎብኘት ሞክሩ፡፡

ከዚህ በታች በጋሞ ዙሪያ የሚገኙ ተፈጥሯዊ ቦታዎች ስም እና ምስል ተቀምጧል፡፡



ምስል 3.5: የነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክ እና የአባያ ሐይቅ /አርባ ምንጭ/

## መልመጃ 2

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ**

1. ልጆች የተፈጥሮ መስህብ ናቸው የምንላቸው ምን አይነት ቦታዎችን ነው?
2. የአባያ እና የጫሞ ሀይቆች በየትኛው የኢትዮጵያ ክፍል እናገኛቸዋለን?
3. የነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ የሚገኘው በየትኛው የኢትዮጵያ ክፍል እናገኘዋለን?
4. የተፈጥሮ መስህብ ያላቸውን ቦታዎች መጎብኘት ምን ጥቅም አለው?
5. የተፈጥሮ መስህብ ያላቸውን ቦታዎች መጠበቅ እና መንከባከብ ምን ጥቅም አለው ትላላችሁ? አስረዱ፡፡



ምስል 3.6: ከፊት ለፊት የነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክ መሃል የእግዜር ድልድይ በስተ ግራ የአባያ ሐይቅ በስተ ቀኝ የጫሞ ሐይቅ



ምስል 3.7: ኮንሶ የሚገኘው ኒው ወርክ የተባለው ተፈጥሯዊ ቦታ



ምስል 3.8: ኮንሶ የሚገኘው ኒው ወርክ የተባለው ተፈጥሯዊ ቦታ

## 3.1.3. በጉብኝት ወቅት እንዴት ዘገባዎችን መፃፍ ይቻላል

ባህል ከሚገለጽባቸው እና ከሚተዋወቅባቸው መንገዶች አንዱ የሆነው የእይታ ጥበብ ነው፡፡ በዚህ የእይታ ጥበብ በሀገራችን የሚገኙ ጠቃሚ የሆኑ ባህላዊ እሴቶችን መዝግቦና ቀርጾ በማስቀረት (በማስቀመጥ) ካለፈው ትውልድ የተላለፉትን የእይታ ጥበባትና የተለያዩ የኪነ-ጥበብና የሥነ-ጥበብ ውጤቶች ከአሁኑ እና ዘመኑ ከደረሰበት ስልጣኔ ደረጃ አንጻር ጎን ለጎን በማስኬድና በማስቀመጥ የማህበረሰቡን የአኗኗር ፣ የአለባበስ ፣ እንዲሁም የቤት አሰራራቸውን ጨምሮ በተለያዩ የእይታ ጥበባትና የኪነ-ጥበብና የሥነ-ጥበብ አመዘጋገብ የማስተዋወቅ ስልት ነው፡፡ ቀርጾ በማስቀመጥ እንደ ቅርስና እንደ ታሪክ ዐውድ ከዘመን ዘመን እንዲሻገርና ትውልድ እንዲያውቀው በመማድረግ ተማሪዎችም ባህላዊ እሴትንና ታሪክን መንከባከብና መጠበቅ ብሎም መጎብኘት እንዲችሉ መማርና ማወቅ አለባቸው፡፡

### የማንቂያ ጥያቄ፡-

1. ልጆች ከአሁን በፊት ስለጎበኙት ቦታ ቀድመው የያዙትን ማስተዋሻ በመጠቀም በዘገባ ወይም በደብዳቤ መልኩ አጭር ፅሁፍ በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችውእንዲያነቡ ማድረግ፡፡

## 3.1.4. ሃገረ-ሰባዊ ድራማዎችን በስነ-ጥበብ መቃኘት

በአካባቢያችን በርካታ ለድራማ የሚሆኑ ታሪኮች ድራማ (ድርሰት) እንዳሉ ይታወቃል፡፡ እነዚህን ሀገር በቀል ድርጊያዎችን በጥበብ በቃኙና ለተመልካች በቀርቡ ከፍተኛ አስተዋፆ አላቸው፡፡ የጋሞ ማህበረሰብ የዕርቅ ስነ-ስርዓት የዱቡሻ ስርዓት ማህበራዊ ፈያዳው ከፍተኛ ነው፡፡

### ዱቡሻ

ዱባሻ በመባል የሚታወቁት ባህላዊ አደባባዮች የመንደሩ ልዩ የባህል እና አገር በቀል እውቀት አንዱ ነው፡፡ ዱቡሻዎች ለጋሞ የተለያዩ ማኅበራዊ እና ባህላዊ ገጽታዎቻቸውን ለመሰብሰብ እና ለማካፈል የሚገለገሉባቸው ትልቅ ቦታዎች ናቸው፡፡

የማህበረሰብ ጉዳዮችን ሆን ብለው ሰዎች ተሰብስበው የሚሰበሰቡበት ቦታ

ነው:: ለምሳሌ ዱቡሻ በዋናነት የአንድ መንደር ነዋሪዎች ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሀገር ሽማግሌዎች የሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታ ሆኖ ያገለግላል:: እንዲሁም ለቅሶ ልምዶች እና ለማህበራዊ ፣ ባህላዊ ክብረ በዓላት እና ሃይማኖታዊ በዓላት ለማክበር የሚውል ቦታ ነው::

በጋሞ ማህበረሰብ ውስጥ ላካ ዱቡሻ በተለይ ልዩ እና በጣም የተከበረ ቦታ ነው:: በዓመቱ ውስጥ የማህበረሰብ ስብሰባዎችን በተለያዩ ገጽታዎች ያስተናግዳል:: እንዲሁም ከዚህም በላይ በዓመት አንድ ጊዜ የመስቀል ክብረ በዓልን በማሳተፍ ሁሉንም ማህበረሰብ ያስተናግዳል:: ይህ ቀን በአከባቢው ማህበረሰብ ላካ ቃማ ወይም የላካ ቀን ተብሎ ይጠራል::

በዚህ ቀን ሁሉም አስራ ሁለቱ ቀበሌዎች ተሰብስበው መስቀልን ለማክበር ተሰባስበው በጣም በሚያነቃቃ እና በሚያስደስት ሁኔታ በመጨፈር እና በመዘመር ያሳልፉታል::

በተጨማሪም በዚህ ቀን የፖለቲካ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጉዳይ የውይይት ልምዶች የከናወኑበታል:: ከዚህ አንፃር ፣ በማህበረሰቦች መካከል ግጭቶች ከተነሱ ፣ ባህላዊ የግጭት አፈታት ወይም ድርድር የሚከናወነው በዚህ ቦታ እና ቀን በመንደሩ ሽማግሌዎች ነው::ይህ የዱቡሻ ቦታ ለመንደሩ ነዋሪዎች አንድነትን ፣ ደስታን ፣ ሰላምን እና ደህንነትን ለረዥም ጊዜ ለመጠበቅ ትልቅ ትርጉም አለው:: በተጨማሪም በዚያ ቦታ የተከናወነው ባህላዊ እንቅስቃሴ የመንደሩን ነዋሪዎች የቆዩ ባህሎችን ፣ ደንቦችን እና ወጎችን ለቀጣይ ትውልድ በዘላቂነት ለመጠበቅ እና ለማስተላለፍ የበኩላቸውን ሚና ይጫወታል:: ይህ ባህላዊ አደባባይ ቦታ ለጋሞ ሰዎች የማንነት ምንጭ ፣ መስተጋብር እና ትስስር ሆኖ በማገልገል ለመንደሮቹ ትልቅ ማኅበራዊ-ፖለቲካዊ እሴት አለው::

## 3.1.5. ሀገረሰባዊ (ሀገረ በቀል) ባህላዊ ድራማዎች

ሀገረሰብ ማለት አንድ አካባቢ የሚኖሩ ቡድኖች አምነው ተማምነው ሚከውኑት ነው:: ባህል በጣም ጥሩ የሚባሉ ለሰው ልጆች ሁሉ አስፈላጊ ነገር ነው:: ተግሳፅ ምክር ውገዛ መሰል ያሉበት ድራማዊ ክንዋኔዎች ያሉበት ነው::

**መልመጃ 6**

1. ሀገር በቀል ድራማ ምንድነው?
2. ዱቡሻ ማለት ምንድነው?
3. በዱቡሻ ምን ምን ይደረጋል?

## የምዕራፍ ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ የበርካታ ባህል እና የተፈጥሮ መስህቦች ያሉባት ሀገር ናት፡፡ እነዚህንም የባህል እና የተፈጥሮ መስህቦች በተለያዩ የሃገራችን ቦታዎች እናገኛቸዋለን፡፡

ኢትዮጵያ በዓለማችን እጅግ ጥንታዊ የስልጣኔ ታሪክ ያላት ክርስትናን እና እስልምናን፣ የዋቄፈና እምነትን ጨምሮ የበርካታ ሀይማኖት ተከታዮች በፍቅር እና በአንድነት የሚኖሩባት ድንቅ አገር ናት፡፡ በቅድመ ሰው ዘር ጥናትም የመጀመሪያ የሰው ዘር መኖሪያ /መገኛ/ ፣ ቡናን ለዓለም ያስተዋወቀች የበርካታ ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሯዊ ቅርሶች ባለቤት የሆነች አገር ናት፡፡

አገራችን በተለየ ሁኔታ የቋንቋ እና የባህል ብዝሃነት የሚታይባት ባህላዊ እና ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤዎች በኪነ-ጥበብ ፣ በስነ-ጥበብ እና በእደ-ጥበብ አዋዝታ ማራኪ ዕይታዎችን የፈጠረች አስደናቂ እና አስደማሚ አገር ናት፡፡ ለዚህም የሥልጣኔ ፣ የባህል እና የታሪክ ባለቤት ለመሆኗም ከአስራ ሁለት በላይ የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ቅርሶች በዓለም አቀፍ መድረክ በዮኔስኮ በማስመዝገብ ታላቅነቱን ያስመሰከረች ሃገር ናት፡፡ ይኽም የሰው ልጆች ሁሉ ቅርስ የሆኑ ሃብቶችን ያቀፈች የዓለማችን ድንቅ አገር ያደርጋታል፡፡

ኢትዮጵያ ከሷት እጅግ ብዙ የባህል ሀብቶቿ ውስጥ በማይዳሰሱ ቅርሶች ዘርፍ ሙዚቃው እና ውዝዋዜውን እናገኛለን፡፡ በሙዚቃ እና ውዝዋዜ እረገድ ሀገራችን ያላት አቅም ከፍተኛ እና ቀደምት ከሚባሉት የሚመደብ ነው፡፡

## የማጠቃለያ ጥያቄዎች

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ**

1. የጋረዱላ ተራራ በየትኛው የኢተዮጵያ ክፍል እናገኘዋለን?
2. ታሪካዊ ቦታዎችን መጎብኘት ምን ጥቅም አለው?
3. 3) ልጆች የተፈጥሮ መስህብ ናቸው የምንላቸው ምን አይነት ቦታዎችን ነው?
4. 4) የአባያ እና የጫሞ ሀይቆች እና የነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርኮች በየትኛው የኢትዮጵያ ክፍል እናገኛቸዋለን?

# ምዕራፍ አራት

## 4. አድናቆት

### መግቢያ

የትውንና የእይታ ጥበብ አድናቆት ማለት ሁሉንም ታላላቅ ሥነ-ጥበባት የሚለዩትን ሁለንተናዊ እና ጊዜ የማይሽራቸው ባህሪያት እውቀት እና ግንዛቤ መስጠት ማለት ነው፡፡

ሙዚቃ ፣ ዳንስ ፣ ስዕል ፣ ቲያትር እና ሲኒማ እነዚህ ጥበቦች የሰብአዊነትን ጥናት ለመረዳት የሚረዱ የትምህርት ቅርንጫፎች ናቸው፡፡ ሙዚቃ ምናልባት በትውን ጥበባት ሁለንተናዊ ሊሆን ይችላል እና በእያንዳንዱ ህብረተሰብ ውስጥ ሙዚቃ ይገኛል እንዲሁም ሥዕል የፈጠራ መግለጫ ዜይቤ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ የተለያዩ ስራዎች አድናቆትን ሊያገኙ የሚችሉት የማህበረሰቡን ፣ የአካባቢውን ባህላዊ የሆኑ ይዘቶችን ይዞ በሚቀርብበት ጊዜ ነው፡፡ እንዲሁም የተለያዩ ባህላዊ ገፅታዎችን የአካባቢውን መልካም ስራዎችን በማድነቅና ለሌላው አካባቢ ስለ አካባቢው እውቅና መስጠት ነው፡፡

### ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

#### ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ

- ሀገረ-ሰባዊ ጥበባት ፣ ትውን እና የእይታ ጥበባት ምን እንደሆነ ይለያሉ፡፡

- በአካባቢያቸው የሚታወቁ ባህላዊ ዜማዎችን ፣ ዘፋኞችን እና ስራዎቻቸውን ለይተው ይረዳሉ፡፡
- የማህበረሰብ ሙዚቃዎች ምን እንደሚመስሉ ይረዳሉ፡፡

## 4.1. ሀገረሰባዊ ጥበባት በትውን እና እይታ ጥበባት በኢትዮጵያ

### መግቢያ

ጥንታዊው ሰው በዋሻ ውስጥ ሲኖር ሕይወቱ በአንድ ላይ የተመሰረተ እንደ ነበር ጠቋሚ መረጃዎች በዋሻ ግድግዳዎች ላይ ተነድፈው የተገኙ የአዳኙ እና የታዳኙ ስዕሎች የስነ-ጥበብ /የኪነ- ጥበብ/ ውጤቶች ናቸው፡፡ የእለት ተእለት ክንዋኔዎች በግጥም ፣ በእንጉረጉሮ ፣ በትረካ ፣ በስነ-ቃል ፣ በስነ-ስዕል ፣ በስነ-ፅሑፍ እያደገ የሄደው የስነ ጥበብ ዘርፍ ሁሉ የሚያንፀባርቁት ከእውነተኛው ህይወት በመነሳት ነው፡፡

ሀገረ-ሰባዊ እና ባህላዊ ጥበባት ሥር የሰደዱ እና የአንድን ማህበረሰብ ባህልዊ ክንዋኔዎች የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡ እነሱም ከሀገረ-ሰባዊ እና ከባህላዊ ቅርስ መስኮች ጋር የተዛመደ ገላጭ ባህልን ያካትታሉ፡፡ የማይዳሰሱ የባህል ጥበቦች እንደ ሙዚቃ ፣ ባህላዊ ውዝዋዜዎች ፣ ተረት(ትረካ) ፣ ታሪካዊ ምስሎች መዋቅሮች ያሉ ቅርፃችን ያካተታሉ፡፡ በኢትዮጲያ በተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ ሀገረ-ሰባዊ ጥበባትን በማህበረሰቡ በስራ ወቅት የጥበብ እንቅስቃሴ ግጥሙ ፣ ሙዚቃው ፣ ትያትሩ ፣ ባህላዊው ውዝዋዜው ፣ ስነ ህንፃው እነዚህን ከንውኖች በማህበረስቡ መካከል ያለው ጥሩ እና ተግባራዊ ስነ-ጥበብን ያሳየናል፡፡

### ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ

- ተማሪዎች በዘፈን ፣ በዳንስ ፣ በትወና ፣ በነፃ ንድፍ እና በፎቶ ግራፍ ይሳተፋሉ፡፡

- በማህበረሰባቸው አካባቢ የሚዜሙ ቀደምት የባህል ሙዚቃዎችን ምን ይመስሉ እንደነበር ይገነዘባሉ፡፡
- በአካባቢያቸው የሚታዎቁ ባህላዊ ዜማዎችን ፣ ዘፋኞችን እና ስራዎቻቸውን ለይተው ይረዳሉ፡፡
- ተማሪዎች የተለያዩ ዜማዎችን በመጫወት አድናቆት ይሰጣሉ፡፡

## የማነቃቂያ ጥያቄ

1. በአካባቢያችሁ በህብረተሰቡ ዘንድ በጣም ተደማጭ እና ተወዳጅ የሆነ የስራ እና የተለያዩ ኩነቶች ሙዚቃ አለ? ካለ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡላቸው

## 4.1.1. ሀገረሰባዊ የሙዚቃ ጥበባትን ማድነቅ

ሀገረሰባዊ የሙዚቃ ጥበባት የምናልቸው በማህበረሰቡ ወይም በአካባቢው የሚታወቁ የማህበረሰቡን ባህል ፣ ወግ እና ስርዓት የያዘ የአካባቢውን ገፅታ በሚያንፀባርቅ መልኩ እና የሙዚቃ ስራዎቻቸውንም የሚገልፁት በራሳቸው ወይም አካባቢያዊ በሆኑ የሙዚቃ መሳሪያዎች ሲሆን ይህንኑ ስራዎቻቸውን ለሌላው አካባቢ ወይም ለሌላው አለም የሚያሳውቁት ሀገረሰባዊ ጥበባትን በመጠቀም አካባቢው እውቅናን እና አድናቆትን እንዲያገኝ የደረጋሉ፡፡ ስራዎችን የሚሰሩም የማህበረሰቡን ወግ እና ባህል ጠንቅቀው በሚያውቁ እና በማህበረሰቡ ውስጥ በሚኖሩ ሰዎች አልያም የማህበረሰቡን ባህል እና ወግ እሴቱን ጠብቀው ፣ አኗኗሩን የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡ ትክክለኛ የባህል ሙዚቃዎች የተፃፉ ግጥሞችን በሚገባ በማዳመጥ ስለ ማህበረሰቡ ባህልና ወግ ማወቅ ይቻላል፡፡

### ጠቃሚ መረጃ

- ከላይ በመግቢያችን እንደገለፅነው የማህበረሰቡን ወግ እና ባህል የሚገልፁ ብሎም ለስራ እንዲነሳሱ ከተዜሙት ሙዚቃዎች መሃል ስለ ጋሞ ማህበረሰብ አካባቢ ሀገረሰባዊ ያምቤ በሚል ዕርስ

**በደሬ የሙዚቃ ቡድን** የተሰራ የስራ ሙዚቃ(ዘፈን) ከታች የምናየው ይሆናል

## ያምቤ

ስራ ላይ ነን እኛ ስራ ላይ ነን
ስራ ላይ ነን እኛ ስራ ላይ ነን
በስራችን ሀገርን ለማስዋብ
ወደ ሀገር ቤት ቱሪስት ለመሳብ
ተፈጥሮና ሰውን ለማስታረቅ
የህዝባችን ጤናን ለመጠበቅ
ስራ ላይ ነን ይሄው ስራ ላይ ነን
ስራ ላይ ነን እኛ ስራ ላይ ነን
ስራ ላይ ነን እኛ ልማት ላይ ነን
በወዛችን ሀገርን ለማልማት
ከሀገራችን ድህነት ለማጥፋት
ስራ ክቡር መሆኑን ለማሳየት
የፅድቅ ሀገር ኢትዮጲያን ለማየት
ስራ ላይ ነን እኛ ስራ ላይ ነን
ስራ ላይ ነን እኛ ልማት ላይ ነን

**ግጥም፡-** የህዝብ እና አብርሃም ቴጋ
**ዜማ፡-** የህዝብ



ምስል 4.1: በጋሞ ብሄረሰብ ዱሬ የሙዚቃ ቡድን በተጫወቱት የሙዚቃ ቪዲዮ ላይ ያምቤ በሚለው የሙዚቃ ርዕስ በተሰራው የስራ ሙዚቃ የተወሰደ ምስል



ምስል 4.2: በጋሞ ብሄረሰብ ዴሬ የሙዚቃ ቡድን በተጫወቱት የሙዚቃ ቪዲዮ ላይ ያምቤ በሚለው የሙዚቃ ርዕስ በተሰራው የስራ ሙዚቃ የተወሰደ ምስል

## ሙከራ

☆ በአካባቢያችሁ የሚታወቁ ሀገረ-ሰባዊ የሆኑ ሙዚቃዎችን በቡድን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ

**ፍንጭ**

እባክዎ መምህር ተማሪዎች የተለያዩ አካባቢያዊ ሙዚቃዎችን እንዲያጠኑና እንዲያቀርቡ ይርዷቸው

## 4.1.2. ሃገረ-ሰባዊ ስነ-ጥበባትን ማድነቅ

ሀገረሰባዊ ስነ-ጥበባት ሲባል ጥበብ የራሱ የሆነ ቅርፅ ፣ እድገት ፣ ለውጥ እና መሻሻል ሲኖረው ቀደም ባለው ጊዜ ይሳሉ የነበሩ ስዕሎችን ብንመለከት የማህበረሰቡን የተለያዩ ክንዋኔዎችን ለማሳየት ከሚጠቀሙባቸው ቦታዎች የሃይማኖት ስፍራዎች ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ፡፡ በመሆኑም በየቤተ-መቅደሶች የሚገኙ የስነ-ጥበብ ውጤቶችን ብንመለከት የሀገረሰባዊ ስዕል አሳሳል የተላበሱ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን መንፈሳዊ ይዘት ቢኖራቸውም ክብ ፊት ፣ ትላልቅ አይኖች ያሏቸው እና ቀለም አጠቃቀማቸው ኢትዮጵያዊ መልክ መያዛቸው ሀገረሰባዊ የጥበብ አገላለፅ ዘይቤ ስላላቸው ከሌሎች የአሳሳል ዜቤዎች የተለዩ ናቸው፡፡



ምስል 4.3: ሐገረሰባዊ ስዕል

## 4.1.3. ሀገረሰባዊ ዕደ-ጥበባት

### እደ-ጥበብ

እደ-ጥበብ በአካባቢያችን የሚገኙ ማህበርሰቦች ለበዓላዊ እና ለባህላዊ ጠቀሜታ የሚውሉ መገልገያዎች የእደ ጥበብ የተሰሩ የፈጠራ ውጤቶች ናቸው።

**ለምሳሌ፡-** የሸማ ሥራ፣ የሸክላ ሥራ፣ የእንጨት ሥራ፣ የብረታብረት ሥራ ወዘተ...። የመሳሰሉት ማህበረሰቡ ለእለት ኑሮው መገልገያ የሚጠቀምባቸው እና የገቢ ምንጭ ከማግኘታቸው ባሻገር የካባቢያቸውን ዕደጥበብ አሠራራቸው ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር የሚያገናኛቸው በመሆኑ አንደኛው ማህበረሰብ የሌላውን ማህበረሰብ የጥበብን ውበት በማድነቅ የጥበብ ውጤቶችን ይጋራሉ።

**ለምሳሌ፡-** የሸማ ሥራ በጋሞ በአካባቢ ከሚተገበሩ የእደ-ጥበብ ዓይነቶች አንዱ ሲሆን በአካባቢያችን ማህበረሰቦች እና ሌሎች በኢትዮጵያ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ለበዓላት ፣ ለአዘቦት ግዚያት በመልበስ ጥቅም ላይ ይውላሉ።



ምስል 4.4: የእደ-ጥበብ ውጤት ከሆኑት ጥቂቶቹ የሽማ ሥራ አልባሳት

## የሸክላ ስራ

የሸክላ ሥራም በአካባቢያችን ከሚተገበሩ የእደ-ጥበብ ዓይነቶች አንዱ ሲሆን ይህኛው የጥበብ ዓይነት የሚከናወነው በአካባቢያችን ከሚገኝ የሸክላ አፈር በሸክላ ባለሙያዎች ይሠራል፡፡

**ለምሳሌ፡-** የመመገቢያና የመጠጫ ፣ የማብሰያ ቁሳቁሶች አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርገዉ ይሠራሉ፡፡



ምስል 4.5: የእደ ጥበብ ውጤቶች ከሆኑት የሸክላ ሥራ ዓይነቶች ጥቂቶቹ

## የእንጨት ሥራ

የእንጨት ሥራም እንደ ሌሎች የዕደ-ጥበብ አይነቶች በእንጨት ሥራ ባለሙያዎች የሚከናወን የሥራ ዓይነት ነው፡፡ የዚህ ሥራ ውጤቶች በአብዛኛው ለቤት ውስጥ መገልገያ ይዉላሉ፡፡

ለምሳሌ፡-አልጋ፣ ጠረጴዛ፣ ወንበር (መቀመጫ)፣ ቁምሳጥን (የልብስ ማስቀመጫ)፣ ቁምሳጥን (የእቃ ማስቀመጫ)፣ ሙቀጫ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡



ምስል 4.6: ከእንጨት የተሠሩ የቤትውስጥ መገልገያዎች

## የተግባር ልምምድ

- በመጽሐፉ ላይ ያሉ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን በማስመሰል በንድፍ ሳሉ
- በቤታችሁ ያሉ የሸክላ እቃዎችን በንድፍ ሰርታችሁ አሳዩ
- የሸማ ልብሶች ላይ ያሉ ጥለቶችን በንድፍ ሰርታችሁ ለጓደኞቻችሁ አሳዩ

## መልመጃ 2

1. ሀገረሰባዊ ጥበብ የምንላቸው ምንድን ናቸው?
2. የዕደ-ጥበብ ውጤቶችን በዝርዝር ጻፉ?

# ማጠቃለያ

ጥንታዊ ሰው በዋሻ ውስጥ ሲኖር ሕይወቱ በአንድ ላይ የተመሰረተ እንደነበር ጠቋሚ መረጃዎች በዋሻ ግድግዳዎች ላይ ተነድፈው የተገኙ የአዳኙ እና የታዳኙ ስዕሎች የስነ-ጥበብ /የኪነ-ጥበብ/ ውጤቶች ናቸው። የእለት ከእለት ክንዋኔዎች በተውኔት ፣ በግጥም ፣ በእንጉረጉሮ ፣ በትረካ ፣ በስነ-ቃል ፣ በስነ-ስዕል ፣ በስነ-ፅሑፍ እያደገ የሄደው የስነ ጥበብ ዘርፍ ሁሉ የሚያንፀባርቁት ከእውነተኛው ህይወት በመነሳት ነው። ስለዚህም ነው ኪነ-ጥበብ የአንድ ሐገር ህብረተሰብ ባህል እና ወግ እሴት ትስስር የአንድነት እና የልዩነት አርማ ተደርጎ የሚታየው። የገሀዱ አለምን ድርጊት በአዲስ ህይወት በመተካት ከሽኖ እና አስውቦ የሚያቀርበው ከያኒ ደግሞ የህዝብ ሀብት ነው። ታሪክ ሰሪ ቢሞትም ታሪክ እንደማያልፈው ሁሉ የጥበብ ሰው ቢያልፍም ጥበቡ አያልፍም። ለጥበብ ስራው ህያውነት ግን የሃብቱ ባለቤት የሆነው ህብረተሰብ ተቆርቋሪነት ወሳኝ ነው።

ሀገረሰባዊ የዕይታ ጥበባት ስንል በአካባቢያችን የሚገኙ የማህበረሰቡን ባህልና ወግ እሴቶች እና ትውፊቶች የሚንጸባርቁበት ዕደ-ጥበባዊና ሥነ-ጥበባዊ በማህበረሰቡ የተሰሩ የፈጠራ ውጤቶች ማለትም ስዕሎች ፣ ቅርጻቅርጾች፣ የሸመናና የሸክላ ሥራዎች ለሎችም ኢትዮጵያዊ ሥነ-ውበትን የተላበሱ በመሆናቸው ኢትዮጵያ ባላት የእይታዊና ሌሎች ጥበባት ተደናቂና የተለየች ሀገር ያደርጋታል።

ሀገረሰባዊ ጥበባት የምንላቸው በአካባቢችንና በሌሎችም የሀገራችን ክፍሎች በተለያዩ የእደ-ጥበብና የእይታ-ጥበብ ባለሞያዎች የሚተገበር የጥበብ ውጤት ነው።

ሀገረሰባዊ የሙዚቃ ጥበባት የምንለው በማህበረሰቡ ወይም በአካባቢው የሚታወቁ የማህበረሰቡን ባህል ፣ ወግ እና ስርዓት የያዘ የአካባቢውን ገፅታ በሚያንፀባርቅ መልኩ እና የሙዚቃ ስራዎቻቸውንም የሚገልፁት በራሳቸው ወይም አካባቢያዊ በሆኑ የሙዚቃ መሣሪያዎች ሲሆን ይህንኑ ስራዎቻቸውን ለሌላው አካባቢ ወይም ለሌላው አለም የሚያሳውቁት ሀገረሰባዊ ጥበባትን በመጠቀም አካባቢው እውቅናን እና አድናቆትን እንዲያገኝ ያደርጋሉ።

ስራዎችን የሚሰሩም የማህበረሰቡን ወግ እና ባህል ጠንቅቀው በሚያውቁ እና በማህበረሰቡ ውስጥ በሚኖሩ ሰዎች አልያም የማህበረሰቡን ባህል እና ወግ እሴቱን ጠብቀው ፣ አኗኗሩን የሚያንፀባርቁ ትክክለኛ የባህል ሙዚቃዎች የተፃፉ ግጥሞችን በሚገባ በማዳመጥ ስለ ማህበረሰቡ ባህልና ወግ ማወቅ ይቻላል።

እደ-ጥበብ በአካባቢያችን የሚገኙ ማህበርሰቦች ለበዓላዊ እና ለባህላዊ ጠቀሜታ የሚውሉ መገልገያዎች የእደ-ጥበብ የተሰሩ የፈጠራ ውጠቶች ናቸው።

ለምሳሌ:- የሸማ ሥራ፣ የሸክላ ሥራ፣ የእንጨት ሥራ፣ የብረታብረት ሥራ ወዘተ...። የመሳሰሉት ለማህበርሰቡ የእለት ኑሮው መገልገያ የሚጠቀምባቸው እና የገቢ ምንጭ ከማግኘታቸው ባሻገር የአካባቢያቸውን ዕደ-ጥበብ አሠራራቸው ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር የሚያገናኛቸው በመሆኑ አንደኛው ማህበረሰብ የሌላውን ማህበረሰብ የጥበብን ውበት በማድነቅ የጥበብ ውጤቶችን ይጋራሉ።

የሸክላ ሥራም በአካባቢያችን ከሚተገበሩ የእደ- ጥበብ ዓይነቶች አንዱ ሲሆን ይህኛው የጥበብ ዓይነት የሚከናወነው በአካባቢያችን ከሚገኘ የሸክላ አፈር በሸክላ ባለሙያዎች ይሠራል።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**ለሚከተሉ ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነው መልስ ምረጥ**

1. ከሚከተሉት ውስጥ የእደ ጥበብ ውጤት የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. የሸመና ስራ　　ሐ. የሸክላ ሥራ

   ለ. የቤት አሠራር　　መ. ሁሉም

2. ከሚከተሉት ውስጥ ሸክላ ሠራ ውጤት የሆነው የቱነው?

   ሀ. እንስራ　　ሐ. ወንበር

   ለ. ሙቀጫ　　መ. ሁሉም

3. ከሚከተሉት ውስጥ የሸመና ስራ ውጤት የሆነው የቱነው?

   ሀ. ሙቀጫ　　ሐ. ጠረጴዛ

   ለ. እንስራ　　መ. ጋቢ

4. ሀገረሰባዊ ጥበብ የምንላቸው ምንድን ናቸው?

   ሀ. ዕደ-ጥበብ እና የእይታ-ጥበብ

   ለ. ሥነ-ጥበብ

   ሐ. ኪነ-ሕንጻ

   መ. ሁሉም

5. ከሚከተሉት ውስጥ ከእንጨት ሥራ ውጤት ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ. አልጋ

   ለ. ከሰል ማንደጃ

   ሐ. ወንበር

   መ.ድስት

6. ያምቤ ሙዚቃ መልክቱ ስለምንድነው

   ሀ. የሰርግ

   ለ. የስራ

   ሐ. የለቅሶ

   መ. ሁሉም

# ምዕራፍ አምስት

## 5. የቡድን ተግባር (ግንኙነት፤ ተግባቦት እና ተግባር)

### መግቢያ

የትውንና የእይታ ጥበባት ወደ ተሻለ የአዕምሮ እድገት የሚመራ ፣ የሰውን ግንኙነት የሚጨምር ፣ ደረጃን የሚያሻሽል ፣ ማህበራዊነትን የሚረዳ ፣ አልፎ ተርፎም የጭንቀት ደረጃን ስለሚቀንስ የትውንና የእይታ ጥበባት በትምህርት ቤቶች ውስጥ በጣም ወሳኝ ርዕሰ ጉዳይ ነው።

የሙዚቃ ትምህርት በልጆች የቋንቋ ችሎታን ያሻሽላል ያዳብራል። ሙዚቃ አንጎልን ያነቃቃል ፣ እና በተለያዩ ድምፆችና ግጥሞች ፣ ተማሪዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ የቃላት ዝርዝር በቀላሉ ይይዛሉ። ሙዚቃ ለሌሎች ቋንቋዎችን ለመረዳት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይሰጣል። ይህም ለተማሪዎች በተለየ ቋንቋ የመረዳትና የመግባባት ችሎታ መሰረት ይፈጥራል።

የትውን እና የእይታ ጥበባትን ለልጆች ማስተማር ያስፈለገበት አይነተኛው እና ዋነኛው ምክንያት እነዚህ የትውን እና የእይታ ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያላቸው ቅርበት ነው።

የትውን እና የእይታ ጥበባት ትምህርት የልጆችን የሙዚቃ ፣ የትያትር ፣ የውዝዋዜ እና የስዕል ክህሎት ከማዳበሩም ባለፈ በሌሎች የትምህርት አይነቶች

የሒሳብ ክህሎታቸውን ፣ የቋንቋ /የማንበብ እና የመፃፍ/ ክህሎታቸውን ፣ የሳይንስ ክህሎታቸውን ፣ ማህበራዊ ሳይንስ /የእርስ በእርስ ግንኙነታቸውን/ ፣ የታሪክ እውቀታቸውን ወ.ዘ.ተ… ለማዳበር አይነተኛ እና ምርጫ የማይገኝለት ነው።

ሙዚቃ ከፍተኛ የማስታዎስ ችሎታን ያዳብራል። በሚስቡ ዜማዎችና በተለያዩ ድምፆች አማካኝነት ሙዚቃ ከእኛ ጋር የሚቆራኝበት መንገድ ሲኖረው ሙዚቃ በአግባቡ ጥቅም ላይ ሲውል ለመማር ማስተማር ሁነኛ መሣሪያ ነው።

### ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ተማሪዎች በጋራ እና በቡድን ሆነው ስለ ተፈጥሮ ስለ ቀለማት ያዜማሉ ይወዛወዛሉ።
- ተማሪዎች ስለ ወንዞች ፣ ሐይቆች ፣ አዕዋፋት ፣ ከዋክብት ወ.ዘ.ተ ያዜማሉ።

### ማነቃቂያ ጥያቄ

1. ተማሪዎች ስለ ሙዚቃ ፣ ድራማ እና ስዕል ለመምህራችሁ አብራሩ?

## 5.1. የትውንና የእይታ ጥበባት እርስ በርስ ያለው ዝምድና

የትውን እና የእይታ ጥበባት የምንላቸው ሙዚቃ ፣ ስዕል ፣ ትያትር እነዚህ እርስ በርስ የሚያገናኛቸው በጣም በርካታ ነጥቦች ይገኛሉ።

የትውንና የእይታ ጥበባት ሰው ድምፃቸውንና አካላት መልእክት ወይም የስነ ጥበብ መግለጫን የሚያስተላልፉበት የጥበብ ዓይነት ነው። የእይታ ጥበቦች በእይታ መንገዶች። ለምሳሌ፡- ፎቶግራፍ፣ ስዕል፣ ቅርፃቅርፅን በእይታ ጥበብ ውስጥ የሚያስተላልፉበት መንገድ ነው።

የትውን ጥበባት እንደ ቲያትር ፣ የህዝብ ንግግር፣ ዳንስ፣ ሙዚቃ እና ሌሎችም በመሳሰሉት በትውን አማካኝነት ስራቸውንና ስሜታቸውን የሚገልፁባቸው መንገዶች አሏቸው። የትውን ጥበባት ባህላዊ ታሪኮችን በዳንስና ከረጅም ጊዜ

በፊት በመድረክ ላይ ትዕይንቶችን በመገንባት ማሳየት ይችላሉ፡፡

የትውንና የእይታ ጥበቦች እንዲሁ እርስ በርስ ይደጋገፋሉ፡፡ የእይታ ጥበባት፣ ድራማ እና ሙዚቃ በሲኒማቶግራፊ መልክ ሲጣመሩ ለምሳሌ የኪነጥበብ ትሥሥሩ እየጠነከረ ይሄዳል፡፡ በተለያዩ አካባቢዎች የሚሰሩትን ዶክመንተሪ ፊልሞች ብንመለከት የአካባቢውን መልዕክቶችን በድራማ ለማሳየት ፣ የእይታ ምስሎችን እና የሙዚቃ አጃቢዎችን ይጠቀማል፡፡

ስነ-ጥበቡን በመጠቀም ዘጋቢ ፊልሞቹ መረጃዉን በበለጠ በሚያስተጋቡ መንገዶች ለማስተላለፍ በተመልካቾቹ ስሜት ላይ ጉልህ ሚናን ይጫወታል፡፡

የትውንና የእይታ ጥበባት ወደ ተሻለ የአዕምሮ እድገት የሚመራ ፣ የሰውን ግንኙነት የሚጨምር ፣ ደረጃን የሚያሻሽል ፣ ማህበራዊነትን የሚያዳብር፣ አልፎ ተርፎም የጭንቀት ደረጃን ስለሚቀንስ የትውንና የእይታ ጥበባት በትምህርት ቤቶች ውስጥ በጣም ወሳኝ ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡ የትውንና የእይታ ጥበባት ትምህርቶች የሚባሉት ድራማ፣ ስዕል እና ሙዚቃ ተማሪዎች በሚማሩበት ጊዜ እንዳይሰለቹ እና ድበርትን ለማፍረስ ጥሩ መንገድ ነው፡፡ ተማሪዎቹ ዘና እንዲሉ እና ከክፍላቸው እረፍት እንዲያገኙ ይረዳል፡፡

የትውንና የእይታ ጥበባት ተነሳሽነት በመስጠት እና ስሜትን በማሻሻል በአንድ ተግባር ላይ ማተኮር ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## 5.1.1. የእይታ ጥበብ ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለው ዝምድና

ተማሪዎች የእይታ-ጥበብ ከሙዚቃና ከትወና እና ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለው ግኑኝነት ምን ይመስላችኋል? መጀመሪያ የእይታ-ጥበብ ማለትምን ማለት ነው? የእይታ- ጥበብ እንደ ሌሎች የጥበብ አይነቶች የራሱ ሆኑ መገለጫዎች አሉት እነርሱም ንድፎች፤ በእርሳስ የሚሰሩ ስዕሎች፤ በሸራላይ የሚሳሉ ቀለም ቅቦች፤ በወረቀትና በጨርቃጨርቆች ላይ የሚሰሩ ህትመቶች፤ ባለሁለት አውታረመጠን ዝርግ ቅርፃች እና ባለ ሦስት አውታረመጠን ቅርጾች ሲሆኑ በአጠቃላይ ከትውን ጥበብና ከሙዚቃ እንዲሁም ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር በቀጥታ ይገናኛል፡፡ ለምሳሌ በተፈጥሮ ሳይንስ፤ በማህበረሰብ ሳይንስ፤ አካባቢ ሳይንስ፤ በቋንቋ እና በሌሎችም የትምህርት ዘርፎች

የእይታ-ጥበብ የትምህርቱ ምስላዊ (ሥዕላዊ )ገላጭ በመሆን የትምህርት መርጃ መሣሪያ ከመሆኑም ባሻገር ጠቃሚና አጋዥ መረጃን በመስጠት ተማሪዎች ትምህርቱን በቀላሉ እንዲረዱ ያደርጋል:: በመሆኑም ተማሪዎች በተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት ውስጥ ስለ አበባ በሚማሩበት ወቅት የተለያዩ የአበባ አይነቶችና አፈጣጠራቸው እንዲሁም ዘራቸውም የተለየ በሆኑ እያንዳንዱ የየራሱ ዉበት አለው:: በመሆኑም ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚያዩዋቸውን የአበባ አይነቶች ስእል በመሳል፣ቀለም በመቀባት የአበቦችን መልክ በማስመስል እይታ ጥበብን ከተፈጥሮ ሳይንስ ጋር ያለውን ቁርኝት ይገልጻሉ:: ከሙዚቃ ጋርም ስለ አበቦች ውበት የተዘፈኑ ዘፈኖችን ወይም መዝሙሮችን በመዘመርና በእንቅስቃሴ በመግለጽ ሙዚቃ ከተፈጥሮ ሳይንስ ጋር ያለውን ቁርኝት ወይም ግንኙነት ያሳያል:: በተጨማሪም ከትውን ጥበብ ጋር ተማሪዎች ለክፍል ጓደኞቻቸው አጠር ያለ ድራማ በማዘጋጀትና በማሳየት ለምሳሌ እንደ ሠርገኛ በመተወን አበባም በሠርግላይ ያለውን መልእክት በመግለጽ ተማሪዎች ስለአበባ ያላቸው ግንዛቤ የሰፋ ከመሆኑም በላይ የተሻለ ዕውቀትን ያገኙበታል:: በመሆኑም የእይታ ጥበብ ፣ ሙዚቃ እና የትወና ጥበብ እንደ ተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት ሁሉ ሌሎችም የትምህርት አይነቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ስለሚገናኙ ተማሪዎች ትምህርታቸውን እየተዝናኑ ከመማር ባሻገር ዕውቀትን በቀላሉ ይገበያሉ::

### መልመጃ 5.1

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ**

1. የእይታ- ጥበባት እነማናቸው?
2. ንድፍና ቀለም ቅብ በምን ዘርፍ ይመደባሉ?

## 5.1.2. ሙዚቃ ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለው ዝምድና

ሙዚቃን ከተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች ጋር ልናገናኝ እንችላለን:: ከሁሉም በፊት ተማሪዎች ወደ ክፍላቸው እንደገቡ አእምሯቸው እንዲነቃቃ ሙዚቃን መጫወት ይመከራል:: እንዲሁም ደግሞ ተማሪዎች የሙዚቃን ግጥሞች ቶሎ የመያዝና ያለመርሳት አቅም ስላላቸው የተለያዩ የትምህርት ዓይኖችን

በሙዚቃ ማስተማሩ ይመረጣል ለምሳሌ ለአካባቢ ሳይንስ ትምህርት ስለ አካባቢ ፅዳት፣ስለ እፅዋት እና ስለተለያዩ አካባቢ ሳይንስ ትምህርትን ስለሚያካትቱ ርዕሶች በሙዚቃ በሚገባ ማስተማር ይቻላል፡፡ ሌላው የትምህርት ዓይነት ደግሞ በሂሳብ ትምህርት ተማሪዎች በቀላሉ ስለ ሂሳብ ስሌቶች ስለ መደመር፣መቀነስ፣ማካፈል እና ማባዛት በሙዚቃ ቢማሩ የተሻለ የመረዳት አቅም ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም ስለ ስነ-ህይወት ተማሪዎች ስለ ግል ንፅህናቸው፣እና ስለ ሰውነት ክፍላቸው በሙዚቃ ሲማሩ በተሻለ ሁኔታ ስለ ትምህርቱ ይረዳሉ፡፡ እናም ለተማሪዎች ከላይ በጠቀስናቸው የትምህርት ዓይነቶች እና ከተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች ሙዚቃን በማካተት ትምህርታቸውን እንዲረዱ ማድረግ ይመረጣል፡፡

## መዝሙር 1

**የስሜት ህዋሳት**

ማነው የሚያውቅ አምስቱን የስሜት ህዋሳት
ማነው የሚያውቅ አምስቱን የስሜት ህዋሳት
ዓይን፣አፍንጫ፣ጆሮ፣ምላስ እና እጅ ናቸው
ዓይን አፍንጫ ጆሮ ምላስ እና እጅ ናቸው
ማነው የሚያውቅ ጥቅማቸውን የስሜት ህዋሳት
ማነው የሚያውቅ ጥቅማቸውን የስሜት ህዋሳት
በዓይናችን እናያለን በአፍንጫችን እናሸታለን
በጆሯችን እንሰማለን በምላሳችን እንቀምሳለን
በእጃችን እንዳስሳለን ነገሮችን እንለያለ

## መዝሙር 2

**መማር እወዳለው**

ትምህርት ቤት መሄድ እኔ እወዳለሁ
ተማሪ ነኝ እኔ መማር እወዳለሁ
መምህሬን እሰማለሁ መምህሬን እሰማለሁ

ጎበዝ ስለሆንኩኝ ሁሌ አጠናለሁ

ማጥናት እወዳለሁ ማጥናት እወዳለሁ

ከጥናት በኋላ እኔ እጫወታለሁ

መጫወት እወዳለሁ መጫወት እወዳለሁ

እናትና አባቴን በስራ አግዛለው

እናቴን እወዳለሁ አባቴን አወዳለሁ


ታላቅ የሚለኝን እኔ እሰማለሁ

**ለምሳሌ:-** ሙዚቃን ከአካባቢ እና ከግል ንፅህናችን ጋር ስናዛምደው የሚመለከተውን መዝሙር እንዘምራለን

## መዝሙር:- 3

**ንጽህናዬን እጠብቃለሁ**

ንጽህናዬን እጠብቃለሁ (2 ጊዜ)
ይህን በማድረጌ እደሰታለሁ (2 ጊዜ)
ሁል ጊዜ! ሁል ጊዜ!
ጠዋት ተነስቼ እጄን እታጠባለሁ፤
ፊቴንም አታጠባለሁ፤
ጥርሴን እቦርሻለሁ፤
ሁልጊዜ! ሁልጊዜ!
ከመብላቴም በፊት እጆቼን እታጠባለሁ፤
ሁልጊዜ! ሁልጊዜ!
ከበላሁም በሁዋላ እጆቼን እታጠባለሁ፤
ሁልጊዜ! ሁልጊዜ!
ንፅህናዬን እጠብቃለሁ(2 ጊዜ)
ይህንበማድረጌ እደሰታለሁ(2 ጊዜ)



**የመዝሙሩ ዜማና ግጥም፡- ውቤ ካሣዬ**

## መዝሙር 4

**ንፅህናችንን እንጠብቅ**

አካባቢን እናፅዳ ዘወትር
ከበሽታ ርቀን ለመኖር
ሁል ጊዜ እናጽዳ ደጃችንን
ንቁ ብርቱ ዜጋ እንድንሆን
በሣሙና እንታጠብ እጃችንን
ተላላፊ በሽታ እንዳያመን
በፅዳት በመኖር በሽታን እንግታ
ጤናችን ይጠበቅ እንበርታ፤ እንበርታ፤

## መልመጃ 5.2

1. ሙዚቃን ከተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች ጋር በማዛመድ ለክፍል ጓደኞቻችሁ እና ለመምህራችሁ አቅርቡላቸው

## ማጠቃለያ

የትውንና የእይታ ጥበባት ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር በማገናኘት ለልጆች የተለያዩ የትምህርት ዓይነቶችን የማስተማሪያ እና የማስረዳት ሁነኛ መንገድ ናቸው::

የትውን ጥበባት እንደ ቲያትር፣ የህዝብ ንግግር፣ ዳንስ፣ ሙዚቃ እና ሌሎችም በመሳሰሉት አማካኝነት ስራቸውንና ስሜታቸውን እንዲሁም ትምህርታቸውን በሚገባ የሚገልፁባቸው መንገዶች ናቸው::

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተክክለኛውን መልስ ምረጡ**

1. ሙዚቃ ጋር ግንኙነት ያላቸው የትምህርት ዓይነቶች አነማን ናቸው?
   - ሀ/ የተፈጥሮ ሳይንስ
   - ለ/ ማህበራዊ ሳይንስ
   - ሐ/ ቋንቋ
   - መ/ ሁሉም
2. የእይታ ጥበብ ለሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ፋይዳው ምንድነው?
   - ሀ/ ምንም አይገናኝም
   - ለ/ በስእልና በምስል ይገለጻል
   - ሐ/ በሙዚቃና በትወና ይገለጻል
   - መ/ ለ እና ሐ መልስ ናቸው::
3. የእይታ ጥበብ ስእልን በምን በምን ይወክላል
   - ሀ/ በንድፍ
   - ለ/ በቀለም ቅብ
   - ሐ/ በቅርጻ ቅርጽና ህትመት
   - መ/ ሁሉም
4. ከሚከተሉት ውስጥ የእይታጥበብን አይገልጽም
   - ሀ/ ስእል መሳል
   - ሐ/ ቀለምቅብ መስራት
   - መ/ ፎቶማነሳት
   - መ/ መልስ የለም

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ**

1. ሙዚቃ ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ምንም ግንኙነት የለውም
2. በአካባቢያችን የሚገኙ አበባዎችሁሉም ቀለማቸው አንድ ዓይነት ነው
3. የእይታ ጥበብ፤ የትወና ጥበብ ፤ ሙዚቃ ከሁሉም ትምህርቶችጋር ይቆራኛል
4. የትውን ጥበብ በሌሎች የትምህርት ዘርፎች በድራማ መልክ ይገለጻል
5. ሙዚቃ ተማሪዎችን አእምሯቸው እንዲነቃቃ ያደርጋል

# ዋቢ መፅሐፍት


- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ የተዘጋጀ የ1ኛ ክፍል የኤስቴቲክስ ማስተማሪያ መጽሐፍ 1998 ዓ.ም.
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ የተዘጋጀ የ2ኛ ክፍል የኤስቴቲክስ ማስተማሪያ መጽሐፍ 1998 ዓ.ም.
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ የተዘጋጀ የ3ኛ ክፍል የኤስቴቲክስ ማስተማሪያ መጽሐፍ 1998 ዓ.ም.
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ የተዘጋጀ የ4ኛ ክፍል የኤስቴቲክስ ማስተማሪያ መጽሐፍ 1998 ዓ.ም.

# የእይታና የትወና ጥበባት

## የተማሪ መጽሐፍ

## 3ኛ ክፍል

የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ